# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 019 መስከረም 19 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## ኢትዮጵያና ሶማሊያ ቀጠናውን በማረጋጋትና በኢኮኖሚ ልማት ትብብራቸውን ያጠናክራሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ልዑካቸው በፕሬዚዳንት ሐሰን ሼክ መሐመድ ከሚመራው የሶማሊያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ልዑካን ቡድን ጋር የሁለትዮሽ ውይይት አድርገዋል። ሁለቱ መሪዎች በኢትዮጵያ እና በሶማሊያ መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ያላቸውን ፍላጎት እና ቁርጠኝነትን ገልጸዋል። በተለይም የአፍሪካ ቀንድ የተረጋጋ እንዲሆን አብሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ ትኩረት ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያ ከአዲሱ የሶማሊያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ አስተዳደር ጋር በተለያዩ ደረጃዎች ለመሥራት ዝግጁ መሆኗን አረጋግጠዋል፤ በተለይም ለኢኮኖሚ ዕድገት አጽንዖት ሰጥተዋል። ጠንካራ እና የተረጋጋች ሶማሊያ ለኢትዮጵያ ጥንካሬ የሚጠቅም መሆኑንም ገልጸዋል።

የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐመድ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የተሻለች ሶማሊያን ለማስቻል ለተከፈለው መስዋዕትነት አድናቆታቸውን ገልፀው፤ ሁለቱ ሀገራት የሚያጋጥሟቸውን የጋራ ችግሮች ለመፍታት የትብብር አስፈላጊነትን አመልክተዋል።

ሁለቱ መሪዎች በኢትዮጵያ እና በሶማሊያ መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ያላቸውን ፍላጎት እና ቁርጠኝነትን ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያ ከአዲሱ የሶማሊያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ አስተዳደር ጋር በተለያዩ ደረጃዎች ለመሥራት ዝግጁ መሆኗን ማረጋገጣቸውን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ኢትዮጵያና ሶማሊያ የጋራ ጠላታቸውን አሸባሪው አልሸባብን ለማስወገድ በጋራ መሥራታቸው ከምንጊዜውም በላይ የሀገራቱን ጠንካራ የትብብር መንፈስ በተግባር ያረጋገጠ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በጋራ እንደሚሠሩ የተገለጸ ሲሆን የሁለቱን አገራት የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በመሠረተ ልማት፤ በተለይም በመንገድና በኃይል ዘርፎች በጋራ መሥራት

ኢትዮጵያና ሶማሊያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «ሪፖርቱ» ተዓማኒ ያልሆኑ ምንጮችን መጠቀሙ ገለልተኝነቱን ጥያቄ ውስጥ አስገብቷል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የተመድ የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት ያቋቋመው ኮሚሽን «ሪፖርት» ተዓማኒነት የሌላቸውን ምንጮች መጠቀሙና የምርመራ ሥርዓቶችን ተከትሎ አለመሥራቱ የኮሚሽኑን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባ መሆኑ ተጠቆመ።

የሚኒስትሮች ግብረ ኃይል ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ዶክተር ታደሰ ካሳ እንደገለጹት፤ የተመድ የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት ያቋቋመው የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የባለሙያዎች «ሪፖርት» ተዓማኒነት የሌላቸውን ምንጮች መጠቀሙና የምርመራ ሥርዓቶችን ተከትሎ አለመሥራቱ የኮሚሽኑን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ አስገብቷል።

እንደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ገለጻ፤ ከመረጃ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ብዙዎቹ የኮሚሽኑ መደምደሚያዎች ምንም ዓይነት ማስረጃ ባልተጠቀሰበት ሁኔታ ወይም ተዓማኒነቱ ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባ መልኩ የተሠሩ መሆናቸውንም ገልጸዋል።



ዶክተር ታደሰ ካሳ

«ሪፖርቱ» በተጠቀሱት ተዓማኒነትን በሚያጎድሉ እና የምርመራ ሥርዓቶችን ተከትሎ ያልተሠራ በመሆኑ የኮሚሽኑን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ በሚያስገቡ ሂደቶች የተጠና ጥናት ነው ያሉት አቶ ታደሰ፤ ይህ ደግሞ የፖለቲካ ፍላጎትን ለማስፈፀም የቀረቡ ማስረጃዎች እንጂ ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በመፈለግ መንፈስ የተዘጋጀ ሙያዊ ሪፖርት አለመሆኑን የሚያመላክት ነው ብለዋል።

በመሆኑም መንግሥት፣ የኮሚሽኑን «ሪፖርት» የተወሰኑ ኃይሎች ከኋላ የሚያራምዱትን አጀንዳ ለማስተግበር ሥራ ላይ እንደዋለ ሂደት እና ያን ሂደት ተከትሎ እንደተዘጋጀ ይመለከተዋል ሲሉ ገልጸዋል።

«ሪፖርት» ለሰብዓዊ መብት ከመቆርቆር ሳይሆን የፖለቲካ አጀንዳ ያነገበና የፖለቲካ ፍላጎት ለማስፈፀም የተዘጋጀ በመሆኑ እንደማይቀበለው መንግሥት ያስታውቃል ሲሉ አክለዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ድርጅቱ ኮሚሽኑ ከማቋቋሙ ጀምሮ ሲቃወም መቆየቱን ያነሱት ዶክተር ታደሰ፤ «ሪፖርቱ» በጦርነት ከተጎዱ ሦስት ክልሎች ይልቅ ቁንፅል በሆነ ሥፍራ ላይ ያነጣጠረ እና ስለሂደቶችም ቁንፅል መረጃ ያለው ነው ሲሉ ገልጸዋል።

«ሪፖርቱ» ተዓማኒ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ደርባ ሲሚንቶ
DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ







አቶ ሙሉብርሀን ኃይለ

### አሸባሪው ትሕነግ የዘር ማጥፋት ወንጀልን አጀንዳ የሚያደርገው የዓለምን ማኅበረሰብ ለማደናገር ነው

ገጽ 4

### የአደባባይ በዓላት ባህላቸውን ጠብቀው በዓለም እንዲታወቁ እየተሠራ ነው

ገጽ 4






### የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ፍቅርና ወንድማማችነትን በሚያጎለብት መልኩ ይከበራል

ገጽ 3

# የድምፃዊ ማዲንጐ አፈወርቅ የቀብር ሥነ ሥርዓት ዛሬ ይፈጸማል

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- የድምፃዊ ማዲንጐ አፈወርቅ የቀብር ሥነ ሥርዓት ዛሬ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት በአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይፈጸማል።

የድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅ የክብር አሸኛኘት እና የቀብር አፈፃፀም ዙሪያ አስመልክቶ ለቀብር ሥነ ሥርዓት የተቋቋመው ኮሚቴ ትናንት በሰጠው መግለጫ እንዳለው፤የድምጻዊው ቀብር ሥነሥርዓት በዛሬው ዕለት በአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል 9 ሰዓት ይፈጸማል።

ኮሚቴውን ወክሎ መግለጫውን የሰጠው አርቲስት አረጋኸኝ ወራሽ እንደገለጸው፣ የማዲንጐ ህልፈተ ሕይወት ድንገተኛ በመሆኑ አስደንጋጭ ነው።

በሕይወት ዘመኑ የሠራቸው ሥራዎች ዘመን ተሻጋሪና ለሀገር ትልቅ አስተዋጽዖ የነበራቸው ናቸውም ብሏል።

የአርቲስቱ ሕልፈተ ሕይወት የመላው ኢትዮጵያ ኃዘን ነው ያለው አርቲስት አረጋኸኝ፤ ቀብሩ በዛሬው ዕለት በ9 ሰዓት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይፈጸማል። ከጠዋቱ አራት ሰዓት አስከሬኑ ከቤቱ በመውጣት ወደ አንድነት ፓርክ በማቅናት በቦታው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የሥራ አጋሮቹ በሚገኙበት የክብር ሽኝት ይደረግለታል።

ሌላው የኮሚቴው አባል ጋዜጠኛ ሰይፉ ፋንታሁን ሚዲያዎች ትክክለኛ መረጃ ማስተላለፍና ማዲንጐን በሚመጥን መልኩ ሥርዓተ ቀብሩ እንዲፈጸም ማድረግ አለባቸው ብሏል። ለዚህም አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉንም ጋዜጠኛ ሰይፉ ገልጿል። ኮሚቴው የሥራ አጋሮቹና አድናቂዎቹ በስፍራው በመገኘት ሥርዓተ ቀብሩን እንዲያስፈጽሙ ጥሪ አቅርቧል።

**ወርቃማው ድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅ ሲታወስ**

አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ አዘዞ ተወልዶ በሦስት ወሩ ወደ ደቡብ ጎንደር ዞን ደብረታቦር ከተማ ሄዶ እዚያው አደገ። አብሮት የኖረው ስሙ ማዲንጎ ይሁን እንጂ ፥ እናትና አባቱ ያወጡለት መጠሪያ ስም "ተገኔ" ነበር፤ "ጠበቃዬ ፥ ጋሻ መከታዬ ማለት ነው" ብሎ ነበር ራሱ ማዲንጎ።

ማዲንጎ በተለያዩ ጊዜያት ባደረጋቸው ቃለ ምልልሶች አባቱን ጨምሮ አብዛኛው ቤተሰቡ የቤተ ክህነት አገልጋይ የነበሩ መሆናቸውን ተናግሯል። በልጅነቱ የሙዚቃ ፍቅር እንዳደረበት ይናገር የነበረው ማዲንጎ፥ የሰባተኛ ክፍለ ጦር ካምፕ የ603 ኮር የሙዚቃ ቡድን ልምምድ ሲያደርግ ከተመለከተ በኋላ ድምጻዊ መሆን እችላለሁ በማለት እድል እንዲሰጡት ጠይቆ እንደነበርም ነው በቃለ ምልልሶቹ የተናገረው።

እናም በወቅቱ እድሉን አግኝቶ የድምፃዊ ኤፍሬም ታምሩን "ና ተላክ ልቤ ፥ ልላክህ ልስደድህ ልቤ" የተሰኘውን ሙዚቃ ተጫውቶ አድናቆት ተቸሮታል።ተቀባይነትን አግኝቶም በዛው በወታደር ቤት ሙዚቃውን የቀጠለ ሲሆን፥ "ማዲንጎ" የሚለው ስሙም እዛው እንደወጣለት ነው የገለጸው።

ማዲንጎ በአንድ ወቅት ኤፍሬም ታምሩን እንደ አርአያ (ሞዴል) የሚመለከተው እና በዋናነትም የኤፍሬም ሥራዎች ወደ ሙዚቃው ዓለም ለመግባት ምክንያት እንደሆኑት እና በብዛት የእርሱን ሥራዎች እንደሚጫወትም ነው ይናገር የነበረው።

በተጨማሪም ሙሉቀን መለሰን፣ ቴዎድሮስ ታደሰ፣ ፀጋዬ እሸቱ፣ አረጋኸኝ ወራሽ፣ ይሁኔ በላይ፣ ኤልያስ ተባባልን እንደሚያደንቅ እና የእነሱን ሙዚቃዎች እንደሚጫወት አውርቷል።

ማዲንጎ በታዳጊ የኪነት ቡድን ከዚያም በወታደር ቤት ብዙ ጊዜን ካሳለፈ በኋላ ኑሮውን ባህርዳር ከተማ በማድረግ ድምፃዊ የመሆን ሕልሙን መስመር አስያዘ።በይፋ ወደ ሙዚቃው ዓለም በተቀላቀለባት ባህር ዳር ከተማም በ120 ብር ወርሐዊ ደመወዝ ተቀጥሮ ቤተሰቡን እያገዘ ይኖር ነበር።

በመቀጠልም ወደ አዲስ አበባ ከተማ በመምጣት የተለያዩ የሙዚቃ ባንዶችን በመቀላቀል የታዋቂ ሙዚቀኞች ሥራዎችን በማቀንቀን ተወዳጅነትን አገኘ። በሂደትም በ1987 ዓ.ም "ስያሜ አጣሁላት" የተሰኘውን እና እሱ የልጅነቴና ከሰው ጋር አስተዋወቀኝ የሚለውን አልበሙን ለሕዝብ ጆሮ አደረሰ።

በዚህም አድናቆትን እና የሕዝብ ፍቅርን ሲያገኝ ከዓመታት በኋላ "አይደረግም" የተሰኘውን ሁለተኛ አልበሙን ለሕዝብ በማድረስ ተወዳጅነቱን ከፍ አደረገ። ይህ አልበሙም አይደረግም፣ የአፋሯ ቆንጆ፣ ሰው የለኝም ፣ ማህሌት፣ ሞኙ ልቤ እና ሌሎች ተወዳጅ ዜማዎችን ያካተተ ነው።

ድምፀ መረዋው አርቲስት ማዲንጎ፥ በመልዕክትም ሆነ በይዘት ጠንካራ መልዕክት ያላቸውን በሀገር፣ በፍቅር፣ በትዝታ እንዲሁም በማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በተለያዩ ቅኝቶች አቀንቅኗል።

በተለያዩ የዓለም ሀገራት በመዘዋወርም ለአድናቂዎቹ ሥራዎቹን በማቅረብ በውጭ የሚኖሩ በኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዳጅነትን አትርፏል። በሂደትም "አይደረግም" የተሰኘውን ሁለተኛውን አልበሙን ካወጣ ከስምንት ዓመት በኋላ "ስወድላት" የተሰኘውን ሦስተኛ አልበሙን ለአድማጭ እንካችሁ አለ።

በዚህ የሙዚቃ አልበሙ ውስጥ ላላተርፍ፣ ስወድላት፣ አቅሜን፣ አይሆንልኝም፣ እባክሽ ታረቂኝ፣ ከተለያየን ፣ ውሰጃት፣ ዳኛ፣ ጎዳናው፣ ማተቧ፣ ማርማር የተሰኙና ሌሎች ሙዚቃዎች ተካተዋል። በስወድላት አልበምም በተለያዩ የሙዚቃ ውድድሮች እጩ እንዲሁም "ምርጥ የፍቅር አልበም" ተብሎ መሸለም ችሏል።

**" ተንገበገበልሽ አረረልሽ ሆዴ፣**
**አትራቂኝ በእኔ ሞት አይብዛ መንደዴ፣**
**ያስታርቀን መውደዴ ፣**
**ልመናዬን ስሚኝ ይቅርታሽ ይድረሰኝ፣**
**ጥፋቴን ስመርሳት እኔ አቅም አነሰኝ፤.... "**

የሚለውና በሦስተኛው አልበሙ ውስጥ የተካተተው የፍቅር ሙዚቃው ሕዝብ ልብ ውስጥ ከቀሩ ተወዳጅ ሥራዎቹ ውስጥ የሚጠቀስ ነው።

**"መቼም ከሀገሩ ከቀዬው ርቆ**
**ሰው ከሀገሩ ቢሄድ ርቆ ቢሄድ ርቆ**
**ልቡ ቀልብ ሃሳቡ መች ይረጋል (2x)**
**ልቡ ከሱ መች ሲረጋ መች ሲረጋ ፣**
**የሰው ሀገር የሰው ነው እንደራስ አይሆንም ፣**
**ቢከፋውም ቢቸገርም ቢያዝንም ብቻውን ነው ፤"**

የተሰኘው ስለሚወዳት ሀገሩ ያዜመው ዜማ ደግሞ በተለይም ከሀገር ርቀው በሚኖሩ የሀገሩ ልጆች ዘንድ በእጅጉ ተወዳጅ ነው።እንዲሁም ከአልበሞቹ በተጨማሪ "በላይ"፣ ከብርሃኑ ተዘራ ጋር የተጫወተው "ሰላም ያገር ሰው"፣ ለ"ዓባይ ወይስ ቬጋስ" ፊልም የሠራው ማጀቢያ ሙዚቃ ከሠራቸው ሥራዎቹ ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው ይጠቀሳሉ።

"በማንኛውም ሙያ ውስጥ ያላችሁ ወጣቶች፥ በጥረት እንጂ ከመሬት ተነስቶ የሚመጣ ነገር የለም፤ በድንገት የሚመጣ ነገርም ጠቃሚ አይደለም" በማለት ያስተላለፈው መልዕክትም የሚታወስ ነው። አርቲስት ማዲንጎ አራተኛ አልበሙን ለአድማጮች ለማድረስ በመሥራት ላይ እንደነበርም ነው የተሰማው። አይቀሬው ሞት ድንገት ፈጥኖ ቀደመው እንጂ።

በተለይም ኢትዮጵያ በተፈተነችበት ወቅት እያመመው ግንባር ድረስ በመሔድና በማሰልጠኛ የሚገኙ ምልምሎችን በማነቃቃት የራሱን ታሪክ የሠራ ብርቅዬ አርቲስት ነበር። ግንባር ድረስ በመዝመትም ማዲንጎ አፈወርቅ በወርቃማ ድምጹ አገር ወዳድ ወጣቶችን ሳይሰስት አዝናንቷል።

ለዚህም በቅርቡ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እጅ እውቅና እና ሽልማት ተበርክቶለታል። አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በወጣትነቱ እና ብዙ መሥራት በሚችልበት ዕድሜው ባደረበት ሕመም ምክንያት በትናንትናው ዕለት በሥጋ ተለይቶናል። ሆኖም በምርጥ አይረሴ የጥበብ ሥራዎቹና በፍሬ ልጁ ዘወትር ስናስታውሰው እንኖራለን፥።

አርቲስቱ የአንድ ሴት ልጅ አባትም እንደነበር ኤፍቢሲ ዘግቧል።የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በድምፃዊው ሕልፈተ ሕይወት የተሰማውን ኃዘን በድጋሚ እየገለፀ ለቤተሰቦቹ፣ ለወዳጅ ዘመዶቹና ለአድናቂዎቹ መፅናናትን ይመኛል።



# የንብረት ታክስን ተግባራዊ በማድረግ የገቢ ምንጭን ማሳደግ ያስፈልጋል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሀገርን ሀብት በፍትሐዊነት ለመጠቀም እና መሠረታዊ የመንግሥት አገልግሎቶችን ለዜጎች ለማዳረስ የንብረት ታክስን በማስተግበር የገቢ ምንጭን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ገለጸ።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር የንብረት ታክስን በፌዴራል እና በክልሎች ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል በተከናወነው ጥናት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት በአዲስ አበባ በተካሄደው ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ የዜጎችን ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የንብረት ታክስን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል ። በዚህም የሀገርን ሀብት በፍትሐዊነት ለመጠቀም እና መሠረታዊ የመንግሥት አገልግሎቶችን ለዜጎች ለማዳረስ የንብረት ታክስን በማስተግበር የገቢ ምንጭን ማሳደግ ያስፈልጋል።

የዜጎችን ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የአገሪቱን የድህነት ምጣኔ ለማሻሻል የንብረት ታክስን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ አፈ-ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር ተናግረዋል።

የንብረት ታክስ ግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኩን አስመልክተው መልእክት ያስተላለፉት አፈ-ጉባኤው የንብረት ታክስ ትርጓሜው እና አፈፃፀሙ ከአገር አገር የሚለያይ ቢሆንም ባደጉ እና እያደጉ ባሉ አገራት ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል ብለዋል።

በኢትዮጵያም የሀገርን ሀብት በፍትሐዊነት ለመጠቀም እና መሠረታዊ የመንግሥት አገልግሎቶችን ለዜጎች ለማዳረስ የንብረት ታክስን በማስተግበር የገቢ ምንጭን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል። አጥኚ ቡድኑ ከሁለቱም ምክር ቤቶች እንዲሁም ከፌዴራል እና ከክልል የተውጣጣ መሆኑን አፈ-ጉባኤው አብራርተዋል።

ጥናቱ አገሪቱ ያለባትን የኢኮኖሚ ጫና እና በታክስ ዙሪያ የተደነገጉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች እንዲሁም የሌሎች አገራትን ተሞክሮ ያካተተ እንደሆነም ነው የጠቆሙት።

ከአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ አኳያ የንብረት ታክስን መጣል ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ መሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል ማለታቸውን የዘገበው ኢዜአ ነው።

የንብረት ታክስን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል በተከናወነ ጥናት እና በታክስ ሕግ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለማሰባሰብ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ የሁለቱም ምክር ቤቶች አባላትን ጨምሮ የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

ዜና

# የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ፍቅርና ወንድማማችነትን በሚያጎለብት መልኩ ይከበራል

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡-የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ፍቅርና ወንድማማችነትን በሚያጎለብት መልኩ እንደሚከበር የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊና የቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሁንዴ ከበደ እንደተናገሩት፤ የኢሬቻ በዓል በቀልና ጥላቻ የሚጠየፍበት፣ ፍቅርና ወንድማማችነት የሚጎለብትበት ታላቅ ሕዝባዊ በዓል ነው።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓልም ይህንን በሚያጎለብት መልኩ ለማክበር ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

በዓሉ ከክረምቱ ጨለማ ወደ ብርሃን ያሸጋገረንን ፈጣሪ በፍጹም ልብ በአንድነት የሚመሰገንበት ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ጥላቻ ጠፍቶ ፍቅር የሚነግስበት፣ ከግለኝነት ይልቅ አብሮነት ደምቆ የሚበራበትና በብዙ መልኩ ተራርቀው የነበሩ ሰዎች የሚገናኙበት በዓል መሆኑንም አንስተዋል።

በዓለም ደረጃ እንኳ እንደ ኢሬቻ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ የሚያገናኙ ታላላቅ ሕዝባዊ በዓላት ስለመኖሩ ለመጥቀስ ያስቸግራል።

በዓለም ታላቅ ሕዝባዊ ክብረ በዓል የሚባለው በብራዚል አገር የሚከበር የሪዮ ሕዝባዊ ካርኒቫል በሶስት ሚሊዮን ሕዝብ እንደሚከበርም አብራርተዋል።


አቶ ሁንዴ ከበደ



ኢሬቻ ያለ ዘር፣ ሐይማኖት፣ ብሔርና ጾታ ልዩነት ሁሉን የሚያሳትፍ በዓል ነው። በተለይ ሕዝቡን በማቀራረብ አንድነትንና ወንድማማችነትን ከማጠናከር አኳያ የኢሬቻ በዓል ሚና የጎላ እንደሆነም ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም የኢሬቻ በዓል አከባበርን አስመልክቶ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በዓሉ ወንዝና ተራራ የሚመለኩበት አስመስሎ በዓሉን ለማጠልሸት የሚነዙ ትርክቶችና ብዥታዎች መኖራቸውን የተናገሩት አቶ ሁንዴ፤ እውነታው ግን የኦሮሞ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ለምለምና እርጥብ ሳር በመያዝ ወደ ወንዝ ወይም ወደ ተራራ በመሄድ ለፈጣሪው ምስጋና ሲያቀርብ መቆየቱን አሁንም በዓሉ በነበረው እሴት እየተከበረ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በዓሉ ሁሉም የአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች በሚባል ደረጃ በማሳተፍ እየተከበረ መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊ፤ አንዳንድ ክልሎች በራሳቸው ተነሳሽነት በየክልላቸው የኢሬቻ በዓል እንዲከበር እያደረጉ ያለው ጥረት የሚደነቅና የክልሉ መንግሥት ትልቅ አክብሮት የሚሰጠው ነው። አንድነታችንን የሚጠነክረውና ወንድማማችነታችን የሚያብበው አንዱ የሌላውን ባህልና ወግ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያከብርና እውቅና ሲሰጥ ነውም ብለዋል።

የኢሬቻ በዓል ከአገራዊ አብሮነትና ከወንድማማችነት እሴቱ ባሻገር የአገር መልካም ገጽታ ለመገንባት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ያብራሩት አቶ ሁንዴ፤ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በርካታ ታዳሚዎች በዓሉ ላይ ስለሚገኙ ለአገር እድገት የሚኖረው ሚናም ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

# አሸባሪው ሕወሓት በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን እየተደገፈ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት መሠረታዊ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕጎች ውስጥ አንዱንም ባያከብርም ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በሚያወጣቸው ሪፖርቶች ቡድኑን እየደገፈ ይገኛል ሲሉ የሕግ ባለሙያው አቶ ደረጀ ተግይበሉ ተናገሩ።

የሕግ ባለሙያው አቶ ደረጀ ተግይበሉ እንደተናገሩት፣ ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በኢትዮጵያ ላይ አካሂጃዋለሁ ብሎ ይፋ ያደረገው "የምርምራ ሪፖርት" ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ነው። በሪፖርቱም መንግሥት "ረሀብን እንደጦር መሳሪያ ተጠቅሟል" ሲል ከሷል። ከዚህ በተቃራኒ የትሕነግ መሪዎች በትግራይ ክልል ያለው ችግር በሌላው ክልል ካለው ችግር የከፋ አይደለም ሲሉ በአደባባይ ተናግረዋል።

ይህ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው "ሪፖርት" ግን መሬት ላይ ያለውን እውነት ለመመልከት ያልፈቀደ፤ ሰበሰብኩ ያለው መረጃም በስልክ የተሰበሰበና ተመልሶ ሊረጋገጥ የማይችል መሆኑን ቁጥሮች ይናገራሉ ያሉት አቶ ደረጀ፣ ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ወደ ትግራይ ክልል በብዙ ሺህ ቶን የሚቆጠር ምግብና መድኃኒት ከሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ወደትግራይ ክልል መላኩን ሪፖርቶች እንደሚያሳዩ ተናግረዋል።

ይህንን የእርዳታ እህል ትሕነግ በመዝረፍ ለታጣቂዎቹ እንደሚያድል በጦርነቱ እጃቸውን ከሰጡ ታጣቂዎችና ከተሰበሩ የሽብር ቡድኑ ምሽጎች ውስጥ በተገኙ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል ያሉት የሕግ ባለሙያው፣ ባለፉት 12 ወራት የእርዳታ ቁሳቁስ ይዘው ወደ ትግራይ ከገቡ 6 ሺህ 631 የጭነት መኪኖች ውስጥ 2 ሺህ በላይ የሚሆኑን አለመመለሳቸውም ቡድኑ ምን ያክል ለራሱ እንጂ ለሕዝቡ እንዳልቆመ ያሳያል ብለዋል።

ዘራፊ ቡድኑ ኮምቦልቻ የሚገኘን የእርዳታ እህል ማከማቻ መጋዘን፤ ከግማሽ ቢሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅም ከዓለም አቀፍ ርዳታ ሰጪ ተቋማት ውስጥ ገብቶ የዘረፈ ቢሆንም ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን "መርማሪዎች" ግን ይህንን የመመልከት ፍላጎት የላቸውም ሲሉም ተናግረዋል።

እነዚህ ማስረጃዎች የትኛውም አካል ረሃብን ለጦር መሳሪያነት እንደተጠቀመ ያሳያሉ ያሉት አቶ ደረጀ፣ ይህ ሁሉ ጫና የሚደረገው የኢትዮጵያን መንግሥት ለማዳከምና ትህነግን ወደ ሥልጣን ለመመለስ የሚደረግ ጥረት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በጦርነት ጊዜ ሀገራት መከተል ያለባቸው ሕጎች አሉ ያሉት የሕግ ባለሙያው፣ ዓለም አቀፋዊ የሰው ልጅ መብት ሕግ "ሕፃናት ጥላቻን መማር የለባቸውም" ይላል። ከዚህ አንፃር የአሸባሪው ቡድን አካሄድ ሲታይ ሕፃናትን የመድፈር፣ የአሸባሪነት ሥራና ተግባራትን እንዲለማመዱ የማድረግ ሥራ እየሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ደረጀ ገለፃ፣ ሕፃናትን ጥላቻ ማስተማር በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ሕግ የተከለከለ ነው። ቡድኑ በአማራና አፋር ክልል በሴቶችና ሕፃናት ላይ የፈጸማቸው


አቶ ደረጄ ተግይበሉ

ሰብዓዊ ጥቃቶች ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት "የምርምራ ሪፖርት" ይህን ጥቃት እንደጥቃት አልቆጠረውም።

ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች በተቻለ መጠን የዓለም አቀፍ ሕግን ተከትለው መውጣት አለባቸው ያሉት አቶ ደረጄ፣ ተጣሱ የሚባሉ ሰብዓዊ መብቶች ካሉም በግልጽና በተጨባጭ ማስረጃዎች መክሰስ ይቻላል። ነገር ግን የወጣው ሪፖርት የሀገርን ሳይሆን የአንድን ቡድን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ነው ብለዋል።

"በጦርነት ውስጥ ንጹሓን ዜጎች ዒላማ መደረግ የለባቸውም" የሚል የሰብዓዊ መብት አለ ያሉት አቶ ደረጄ፣ በሪፖርቱ ይህንን ሕግ እንደጣሰ ግን አልገለጹም። ሕፃናትና ሴቶች ላይ ጉዳት የሚያደርስ አካልን መንግሥት ብሎ መጥራቱም አሳፋሪ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ደረጄ ገለፃ፣ ይህ የሚያሳየው ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ በመውጣት የአንድን ሀገር ሉዓላዊነት እየተገዳደረ መሆኑን ነው። በተለይ ኮሚሽኑን ትዝብት ውስጥ የሚከተው የኮሚሽኑ አባል የሆነች ሀገርን ከማዳመጥ ይልቅ አንድ ቡድንን ሲደግፍ መታየቱ በጥቂት ሀገራት ፍላጎት እየተመራ እንደሆነ ያሳያል።

ይህም ሀገራት በኮሚሽኑ ላይ ያላቸው አመኔታ ይቀንሳል ያሉት አቶ ደረጄ፣ በእውነታ ላይ ያልተመሠረቱ መረጃዎችን ከተለያዩ ቡድኖች መቀበል ከአንድ ዓለም አቀፋዊ ኮሚሽን የሚጠበቅ አይደለም ብለዋል።

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ከሕፃናት መብት ጋር በተያያዘ የዓለም አቀፍ የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ የሕፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር፣ ከዚህም ባለፈ ደግሞ ሕፃናት በጦርነት ውስጥ እንዳይከፈሉ የደነገገውን "ኦብሽናል ፕሮቶኮልን" ፈራሚ ናት።

"የሰብዓዊ መብትና ድንጋጌዎችን ማክበር" አንድ ሀገር ጦርነት ውስጥ ብትሆንም የማይጣሱ መብቶች ናቸው። እነዚህ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው ስምምነቶች ጥቂቶቹ ናቸው ሲሉም የሕግ ባለሙያው አብራርተዋል።

ኮሚሽኑ የቅኝ ግዛት ሥርዓትን በእጅ አዙር እንደ ገና የማምጣት ሁኔታ ይታይበታል። ስለዚህ ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን ይፋ ያደረገውን "የምርምራ ሪፖርት" በድጋሚ ሊያጤነው ይገባል ሲሉ የሕግ ባለሙያው አቶ ደረጄ ተግይበሉ አሳስበዋል።



# የጃፓን መንግሥት ለተንቀሳቃሽ የሕክምና ክሊኒኮች አገልግሎት የሚውል ድጋፍ አደረገ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የጃፓን መንግሥት በአርብቶ አደር አካባቢዎች፣ ከድርቅ እና ከጦርነት ጋር ተያይዞ ለሚፈናቀሉና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች የጤና አገልግሎት ሽፋንን ለማጠናከር የሚያግዝ የ185 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ።

የሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር ወይንም የ185 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ስምምነቱን በጃፓን በኩል የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ታካኮ እና በኢትዮጵያ በኩል የፈረሙት ደግሞ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሬታ ሰዋሰው ናቸው።

የተደረገው ስምምነት በአምስት ክልሎች ላይ 10 ተንቀሳቃሽ ክሊንኮች አገልግሎት ተደራሽ እንዲያደርጉ የሚያስችል ሲሆን፤ በአፋር፣ በሱማሌ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በተለያዩ ምክንያት ለተፈናቀሉ ዜጎች አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

በስምምነቱ ወቅት የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ታካኮ ተንቀሳቃሽ የሕክምና ክሊንኮቹ በአምስቱ ክልሎች ላይ ያለውን የጤና አገልግሎት እንደሚያሳድገው እምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል። ድጋፉ በኢትዮጵያ እና በጃፓን ሕዝቦች መካከል ወንድማማችነትን እንደሚያጠናክርም ነው የገለጹት።

ተንቀሳቃሽ ክሊኒኮቹ በሕክምና መሣሪያ የተደራጁ፣ አገልግሎት ለመስጠት ምቹና ኤሌክትሮ ካርዲዮግራፍ፣ አልትራ ሳውንድና ሌሎች ዘመናዊ የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የተገጠሙላቸው መሆናቸውንም አመልክተዋል።

ተንቀሳቃሽ የሕክምና ክሊኒኮቹ በእርግዝና ጊዜ፣ በወሊድ እና በድህረ ወሊድ ወቅት የጤና አገልግሎት ለማዳረስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው እና በአምስቱ ክልሎች 800 ሺህ ለሚገመቱ እናቶችን አገልግሎት እንደሚሰጥ አምባሳደር ኢቶ ታካኮ ጠቁመዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሬታ ሰዋሰው በበኩላቸው፤ ዘመናዊ መሣሪያ የሚገጠምላቸው የሕክምና ክሊኒኮቹ ኢትዮጵያ የጤናውን ዘርፍ ለማሻሻል የምታደርገውን እንቅስቃሴ እንደሚያግዙ ተናግረዋል።

በአርብቶ አደሮች አካባቢ የሚኖሩ የእናቶች እና ሕጻናትን ጤና ለማሻሻል ያላቸው አስተዋጽዖ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፤ የጃፓን መንግሥት የጤና ዘርፉን ለማሳደግ ከዚህ ቀደምም ላደረጋቸውና ለሚያደርጋቸው ድጋፎች ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ፤ በሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ በተለይም የእናቶችና ሕጻናትን ጤና ለማሻሻል እየተሠራ እንደሚገኝ አስታውሰዋል። ተንቀሳቃሽ ክሊኒኮቹ ላለው ችግር በቂ ባይሆኑም አሁን ላለው ሁኔታ አስተዋጽዖ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች የሕክምና ቁሳቁስ እጥረት መኖሩን የጠቀሱት ሚኒስትሯ ከጃፓን መንግሥት የተገኘው ድጋፍ ይህን ክፍተት ይሞላል ነው ያሉት።

የእናቶችና ሕጻናት ጤና ተደራሽነት ላይ የፍትሐዊነት ችግር ያለበት፣ እስከዛሬ በታዩት ለውጦችም በበቂ ሁኔታ ውጤት ያልታዩባቸው የአርብቶ አደር ክልሎች ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

ተንቀሳቃሽ ክሊኒኮች የእናቶችና የሕጻናትን ጤና በማሻሻልና የሞት ምጣኔን በመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተገልጿል። የጤና አገልግሎትን በፍትሐዊነት ለማዳረስ ያግዛልም ተብሏል።

ተንቀሳቃሽ ክሊኒኮቹ በሕክምና መሣሪያ የተደራጁ፣ አገልግሎቱ ተደራሽ በሚደረግባቸው ክልሎች በርካታ እናቶችና ሕጻናትን ሕይወት እንደሚታደግና የጤና አገልግሎቱንም እንደሚያሳድግም ነው የገለጹት።

# አካል ጉዳተኞቹ የሜዳሊያ ተሸላሚዎች

**ሞገስ ተስፋ**

ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተያይዘው ከሚመጡ ብዙ ፈተናዎች፣ ውጣ ውረዶች፤ የገጠማቸውን ፈታኝና ተስፋ አስቆራጭ ጊዜያት በጽናት አልፈዋል። ዛሬ ለብዙ አካል ጉዳተኞች አርዓያ መሆን የሚችል ስኬት ላይ ደርሰዋል። የይቻላል ተምሳሌት ሆነዋል። በጎንደር ዩኒቨርስቲ የ2014 ዓ.ም በሕግ ትምህርት ቤት በማዕረግ ተመርቀው ሜዳሊያቸው ከአንገታቸው አጥልቀዋል። አካል ጉዳተኝነት ሕልምን ከማሳካት እንደማያግድ ብርሃናቸውን በሰፊው አብርተው ለብዙዎቹ በተምሳሌትነት የገለጡ የይቻላል ዓርማዎች በጎንደር ዩኒቨርሲቲ በሕግ ትምህርት ቤት በከፍተኛ ማዕረግ የተመረቁት ጌታው የሻምበልና ስንዱ አለፈው ናቸው።

ተማሪ ስንዱ አለፈው በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሕግ ትምህርት ክፍል የ2014 ተመራቂ ስትሆን 3 ነጥብ 39 በማምጣት የሜዳሊያ ተሸላሚ ናት። ስንዱ፤ እንደ አገር በአካል ጉዳተኞች ላይ ያለው ችግር ከፍተኛ ነው ። አይነ ስውር ብሆንም ፈጣሪ ብርሃን ይሰጣል፤ ፈተናውን ተቋቁሜ በመማር በከፍተኛ ውጤት መመረቄ ለእሷ ብቻ ሳይሆን ሳይማር ላስተማረኝ አርሶ አደር አባቴ ትልቅ እድልና ድል ነው ብላለች።

እንደማንኛውም የገጠር ልጅ በገጠር የሚሠሩ ሥራዎችን በመሥራት እንዳደገች የምትገልጸው ተማሪ ስንዱ፤ ሳይማሩ ከተማሩት በላይ ድጋፍ በማድረግ ውጤታማ እንድትሆን የአባቷ ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቁማለች። በማስተርካርድ ፋውንዴሽን ድጋፍ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት ማኅበረሰብ አጋዥነት በጥረቷ ስኬት እንዳስመዘገበችም ትናገራለች።

በቀጣይ በሙያዋ የበርካታ አካል ጉዳተኞች ችግር እንዲፈታ የምትገልጸው የማዕረግ ተመራቂዋ፤ በቻለችው መጠን አካል ጉዳተኝነት ሊመጣ የሚችልባቸው ነገሮችን መቀነሻ መንገዶችን ማሳየት፤ ከምንም በላይ ደግሞ በሀገር ሰላም እንዲኖር ሰፊ ሥራ እሠራለሁ ብላለች። በሕግና በፖሊሲ ቀረጻ በኩል የሚሠሩ ሥራዎች አካል ጉዳተኞችን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ የበኩሏን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁ መሆኗንም ተናግራለች።

ብዙ አካል ጉዳተኞች የትምህርት እድል ስለማያገኙ ዕድሉን እንዲያገኙ አርአያ ሆና እንደምትሠራ የገለጸችው ስንዱ፤ ጥራት ያለው ትምህርት ቤትና ትምህርት ላይገኝ ይችላል፣ ነገር ግን ዋናው ነገር ለራስ እችላሁ የሚለውን ሀሳብ መንገር ነው። በቀጣይ ዓቃቤ ሕግ በመሆን ለማገልገል ፍላጎት አለኝ ስትል ገልጻለች።

ሌላው በጎንደር ዩኒቨርሲቲ በሕግ ትምህርት ቤት 3 ነጥብ 59 በማምጣት የሜዳሊያ ተሸላሚ የሆነው ደግሞ ጌታው የሻንበል ነው። ጌታው እንደሚለው «የአካል ጉዳት ሳይደርስብኝ ስለትምህርት ብዙም ትኩረት አልሰጥም ነበር። አካል ጉዳት ከደረሰብኝ በኋላ እችላለሁ በማለት ትኩረቴን ትምህርት ላይ አድርጌአለሁ። ለስኬቴ ምንጩ እልህና እችላለሁ የሚለውን ለራሴ በመንገሬ ነው» ብሏል።

ጌታው እንደሚለው በማኅበረሰቡ ውስጥ አካል ጉዳተኞችን ዝቅ አድርጎ የማየት አስተሳሰብ አለ። «ተመርቄ ጋዋን ለብሼ መድረክ ላይ ሽልማት ስወስድ በጥረቴ ያገኘሁት ውጤት ሳይሆን በልመና የተገኘ ውጤት እንደሆነ ሁሉ የሚያስብ አለ። በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ቁጭትና እልህ በውስጤ ስላለ በርትቼ በማጥናቴ ውጤታማ ሁኛለሁ» ብሏል።

«እኔ እችላለሁ፣ እሠራለሁ፣ ራሴን ቤተሰቤን፣ አካባቢዬንና አገሬን መቀየር እችላለሁ» በማለት የገለጸው ጌታው፤ አርኣያ የሆነችው በዊልቼር የምትጓዝ አንዲት ፓኪስታናዊ አካል ጉዳተኛ መሆኗንም ይናገራል።

“እኔ ችሎታን አያለሁ፤ ሰዎች ደግሞ አለመቻሌን ያያሉ” የምትለው የዚህች ፓኪስታናዊ ንግግር፤ እኔም አንድ እግሬ ተጎድቷል፣ እኔ የማየው አካል ጉዳተኛ መሆኔን ሳይሆን እችላለሁ፣ ራሴንና ዓለምን እቀይራለሁ፤ እንደ ጓደኞቼ መሆን እችላለሁ» የሚለውን ነው ብሏል።

ጌታው ሰዎች የራሳቸውን ድክመት በእኔ ለመሸፈን ይሞክራሉ፤ እግር ኳስ መጫወት እችላለሁ፤ ነገር ግን ለምን እንደቻልኩ ሳይሆን እንዴት ይጫወታል ይላሉ። ለምሳሌ የሚዘለል ነገር ካለ ቆይ እኔ እሻላለሁ ይላሉ። ይህ በራሱ አካል ጉዳተኞችን ዝቅ የሚያደርግ አስተሳሰብ ነው። ስለዚህ በጣም የበዙ ፈታኝ እንቅፋቶች አሉ ። ነገር ግን በይቻላል መንፈስ ለዚህ በቅቻለሁ ብሏል።

የሕግ ተማሪው፤ «ነገ ላይ ዳኛ ሆኜ ስፈርድ፣ ነገረ ፈጅ ሆኜ ነገርን ስመለከት፣ ጠበቃ ሆኜ ሰዎችን ስወክል ያኔ ሰው ይችላል ይላል። በአካባቢዬ ከንፈራቸውን የሚመጡ ሰዎች ዛሬ እዚህ ደረጃ ስደርስ ይችላል የሚለውን ይቀበላሉ» ሲልም ተናግሯል። ከዚህ ውጭም ጋዜጠኛ ሆኖ ድምጽ ለሌላቸው አካል ጉዳተኞች ድምጽ ለመሆን ሕልሙ እንዳለው ተናግሯል።

አካል ጉዳተኝነት በእርግማን የሚመጣ አይደለም የሚለው ጌታው፤ እሱም አካል ጉዳት የደረሰበት ሳይክል ሲነዳ መሆኑን በትዝታ ይናገራል። የመገናኛ ብዙኃን ውጤታማ የሆኑ አካል ጉዳተኞችን ወደፊት በማምጣት በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ ማስቆም ይገባቸዋል። ሁሉም ሰው እኩል ነው የሚል አስተሳሰብ በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዲፈጠር ቢሠራ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አካል ጉዳተኞች ከችግራቸው ይወጣሉ ሲል ጠቁሟል።

በኢትዮጵያ 17 ነጥብ 6 የሚሆነው ሕዝብ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ።

# አሸባሪው ትሕነግ የዘር ማጥፋት ወንጀልን አጀንዳ የሚያደርገው የዓለምን ማኅበረሰብ ለማደናገር ነው

**መሰረት ገ/ዮሐንስ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትሕነግ ጦርነቱ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ የዘር ማጥፋት (ጄኖሳይድ) አጀንዳ ማድረጉ ማኅበረሰብ ዓለም ለማደናገርና ለማሳሳት እንደሆነ የትዴፓ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሀን ኃይለ ገለፁ። ያልተናበበው መግለጫ ወታደራዊና ፖለቲካዊ የሕወሓት አመራር ኪሳራ እንደደረሰበት የሚያመላክት እንደሆነም ተጠቁሟል።

አቶ ሙሉብርሀን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤አሸባሪው ትሕነግ ጦርነት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ በትግራይ ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት (ጄኖሳይድ) እየተፈፀመ እንደሆነ፤ ጦርነቱም በትግራይ ሕዝብ ላይ እንደተከፈተ እየገለፀ የቆየበት ምክንያት የዓለም ማኅበረሰብን በማደናገርና በማሳሳት ወደ ስልጣን ለመመለስ የተጠቀመበት አካሄድ ነው ብለዋል።

በሰሜን ክልል እየተካሄደ ያለው ጦርነት ሀገር ለማፍረስ የተነሱ የሕወሓት አመራርና ሀገር ለማዳን እየተንቀሳቀሰ ባለው መንግሥት መካከል ነው ፣ እውነታው ይህ ነው፣ በትግራይ ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት (ጄኖሳይድ) እየተፈጸመ ነው የሚለው የቡድኑ አጀንዳ ማደናገሪያ ነው ብለዋል።

ሕወሓት ከመሐል ሀገር ፖለቲካዊ ኪሳራ ደርሶበት የሄደ ነው ፣ ፖለቲካ ኪሳራ ፖለቲካዊ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ በኃይልና ፖለቲካዊ መንገድ ለማሸነፍ የሞከሩ ናቸው ያሉት አቶ ሙሉብርሀን ፣ ይህ ደግሞ በፖለቲካዊና ወታደራዊ አመራር ትልቅ ክፍተት እንደፈጠረላቸው በሚሰጡት ያልተናበበ መግለጫ መረዳት ይቻላል ብለዋል። ይህ አሸባሪው ሕወሓት ፖለቲካዊና ወታደራዊ ኪሳራ እንደደረሰበት የሚያመላክት እንደሆነም አመላክተዋል።

አንዳንድ የዓለም ሚዲያዎች አሸባሪው ትሕነግ ስልጣን ላይ በነበረበት ወቅት ተላላኪ በሚባል ደረጃ የነሱ ፍላጎት ይፈፅምላቸው ስለነበር የተዛባ ወገናዊነት እያሳዩ ይገኛሉ ያሉት አቶ ሙሉብርሀን ፣ አሁን ያለው መንግሥት ግን የኢትዮጵያን ጥቅም ያማከለ መንግሥት ስለሆነ ይህ አቋም ታሪካዊ የሆኑ ጠላቶቻችን ስለማይፈልጉት ነው ብለዋል። እነሱ የሚፈልጉት ለነሱ የሚላላክ መንግሥት ነው፣ የሚላላክላቸው መንግሥት ለመፍጠር ነው የዓለም ሚዲያዎች ለአሸባሪው ሕወሓት አላስፈላጊ ወገናዊነት እያሳዩ ያሉት ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ጦርነቱ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ዘር ማጥፋት (ጄኖሳይድ) ጎልቶ እንዲወጣ እየሠራ ሲሆን በዚህ ደግሞ የዓለምን ማኅበረሰብ በማደናገር በመንግሥት ላይ ማዕቀብ እንዲጣልና አንገቱን እንዲደፋ ዓላማ ያደረገ እንደሆነ የሚታወቅ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በቅርቡ የሕወሓት ወታደራዊ መሪዎች እርስበርሱ የማይናበብ እና የሚጋጭ ተከታታይ መግለጫ መስጠታቸውም በመካከላቸው ያለመግባባት እንዳለ የሚያመለክት ነው ሲሉም አቶ ሙሉብርሃን አስረድተዋል።

# የአደባባይ በዓላት ባህላቸውን ጠብቀው በዓለም እንዲታወቁ እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሚከበሩ ኃይማኖታዊና ሃገራዊ የአደባባይ በዓላት ባህላቸውን ጠብቀው ለዓለም እንዲታወቁ እና የውጭ አገር ቱሪስቶችን በመሳብ የቱሪዝም ዘርፉን እንዲያሳድጉ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአደባባይ በዓላት የቱሪዝም ዘርፉን ለማነቃቃት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። በዓላቱ በዓለም ቅርስነት መመዝገብ ደግሞ ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ጎልታ እንድትታወቅ ከማድረግ ባለፈ የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝ በማድረግ አስተዋጽዖው ከፍተኛ ነው።

አከባበሩም የአገሪቱን ባህል፣ ታሪካዊና መንፈሳዊ ትውፊቶቿን የምታስተዋውቅበትና ኃይማኖታዊና ኢትዮጵያዊ ባህላቸውን ሳይለቁ ለዓለም ሁሉ እንዲዳረሱ ለማድረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

በዓላቱ የሥራ እድልን በመፍጠር፣ የእርስ በእርስ ትስስርን በማጠናከርና ሰላምን በማስፈን በኩል ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ስለሺ፤ ዘንድሮ ከአምናው በተሻለ የጎብኝዎች የመስቀል ደመራ፣ የወላይታ የዘመን መለወጫ “ጊፋታ”፣ የሃዲያ የዘመን መለወጫ “ያሆዴ”ና የዓለም የቱሪዝም ቀን በመስከረም ወር ከሚከበሩ በዓላት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ ስለሺ፤ እነዚህን በአግባቡ ለቱሪዝም መስህብነት መጠቀም እንደሚገባ ተናግረዋል።

እነዚህ በዓላት በሕዝቦች መካከል ፍቅርን፣ መተሳሰብንና ሀገራዊ አንድነትን ለመፍጠር ትልቅ ፋይዳ አላቸው። በበዓላቱ የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከመሳተፋቸውም በላይ በርካታ የውጭ አገር ቱሪስቶች ይታደሙባቸዋል ብለዋል።

ስለዚህ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚደረጉ የአደባባይ በዓላት አከባበሮችን ወደ መስህብነት ለመለወጥ ከወረዳዎች ጀምሮ እስከ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድረስ ጥረት እየተደረገ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በቅርስነት ከተመዘገቡት በተጨማሪ ሌሎች በዓላትንም በዩኔስኮ ዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። የነዚህ



አቶ ስለሺ ግርማ

በዓላት በአደባባይ የሚከበሩ በመሆናቸውና የማኅበረሰቡ እሴትና ባህል የሚገለጡባቸው በመሆኑ ለቱሪስት መስህብነት በመጠቀም የቱሪስት ዘርፉን ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽዖ አላቸው ብለዋል አቶ ስለሺ።

የነዚህ በዓላት አከባበር የአገሪቷ ሰላምና ደህንነት ሁኔታን የሚያሳይና ኢትዮጵያ ውስጥ የጸጥታ ችግር አለመኖሩን ያሳያል ያሉት አቶ ስለሺ፤ ጎብኚዎች አገሪቷ ያለችበትን ሁኔታ አውቀው በመልካም መንፈስ እንዲመጡ ያደርጋቸዋል ብለዋል።

ለቱሪዝም ዘርፍነት የሚያገለግሉ ሀብቶችን የመለየት ሥራ እየተሠራ ነው። በዚህ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ገጽታ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ማስተዋወቅና ማሳየት ይቻላል ሲሉም ጠቁመዋል።

ተደብቀው የቀሩ ነገር ግን ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያላቸው ሀብቶችን ለመለየት እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ድብቅ የሆኑ የአደባባይ በዓላትን ማስተዋወቅ እንዲቻልና ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆኑ በሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በኩል ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

የቱሪዝም ዘርፉ በኮቪድና በጦርነቱ የተጎዳ በመሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ሳያገኙ ቀርተዋል ያሉት አቶ ስለሺ፤ አብዛኛዎቹ የቱሪዝም መዳረሻዎች ለቱሪስት ዝግጁ በመሆናቸው ሁሉም ሰው ከሌላ ቦታ የሚመጡ እንግዶችን በአግባቡ በመሸኘትና በአካባቢው የሚገኙትን የቱሪስት መስህቦችን በማስተዋወቅ በዓላቱ ጎልተው እንዲወጡ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ሲሉ አመልክተዋል።

# ኢትዮጵያና ሶማሊያ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ምሑራን አስተያየት ይሰጣሉ።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባለፈው ዓመት ሰኔ 2 ቀን 2014 ዓ.ም በአዲሱ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼህ ማሕሙድ በዓለ ሲመት ላይ በሞቃዲሾ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር በሶማሊያ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በመደረጉ መደሰታቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት የጋራ እድገት እና ልማት ትብብር ላይ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በመከተሏ ሁለቱ አገራት በቀጣናዊ ትስስር አዲስ መንገድ መክፈታቸውን መናገራቸው ይታወሳል።

በወቅቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተገኙ ዲፕሎማሲያዊ ድሎች ከአዲሱ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ጋር በጋራ በመሥራት ይበልጥ እንደሚጠናከሩ እና እንደሚሰፋም ነው ያስታወቁት።

የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐመድ ትናንት የሁለት ቀን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ለማድረግ አዲስ አበባ መግባታቸው ታውቋል።በትናትናው ዕለትም የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼክ መሐመድ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደርን (ኢመደአ) ጎብኝተዋል።

# «ሪፖርቱ» ተዓማኒ ያልሆኑ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አማካኝነት የተቋቋመው የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን ሥራዎቹን ሲሠራ በኮሚሽኑ የአሠራር ሥርዓቶች ላይ አለመመሥረቱ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመሰል ጥናቶች መሠረታዊ እሳቤዎች እና ደረጃዎች ላይ ተመሥርቶ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

«ሪፖርቱ» ከገለልተኛነት ጋር የተያያዘ ጥያቄ ጭምር የሚያስነሳ ነው። የማረጋገጫ ደረጃዎችን በተመለከተም ዝርዝር የሆኑ ደረጃዎችን ባላሟላ መልኩ የተዘጋጀ «ሪፖርት» በመሆኑ መንግሥት ሂደቱንም ሆነ ውጤቱን የማይቀበለው መሆኑን አሳውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የበዓላቱ ወንድማማችነትንና አንድነትን በሚያጠናክር መልኩ መከበር የኢትዮጵያውያን ታላቅነት መገለጫ ነው!

ሰላም ለአንድ ማኅበረሰብም ሆነ አገር ዕድገት ዋነኛ መሠረት ነው። ይህን ትልቅ እሴት በመጠበቅም ሆነ በማጎልበት ሂደት ውስጥ መላው ሕዝብ የሚኖረው አስተዋጽኦም ከፍ ያለ እንደሆን ይታመናል። በተለይም ከዘመናት ኋላቀርነት ለመውጣት ህልም አልመን ወደ አዲስ የብልጽግና ጎዳና ለመጓዝ ለምንተጋ ለእኛ ኢትዮጵያውያን ሰላም ለህልማችን ስኬት አልፋና ኦሜጋ ነው።

ኢትዮጵያውያን በሰላም ጉዳይ በየዘመኑ በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ለማለፍ የተገደድን ሕዝቦች ነን፤ ለዚህም ብዙ ዋጋ ከፍለናል፣ አሁንም እየከፈልን ነው። ይህም ሆኖ ግን ስለ ሰላም ካለን ለዘመናት የካበተ መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች አንጻር ዛሬም ቢሆን ስለ ሰላም ቀናኢ ሕዝቦች ነን።

ይህ ጽናት የወለደውና በብዙ ውድ ዋጋ የታጀበው ሰላም ወዳድነታችን ዛሬም ቢሆን የጀመርነውን የብልጽግና ጉዞ አስጠብቆ ለማስኬድ ተጨማሪ ዋጋ እየጠየቀን ነው፤ መላ ሕዝባችንም የሰላሙን ዋጋ በመገንዘብ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለሰላሙ ዘብ ቆሟል። እያንዳንዷን ቀን ስለ ተስፋው አዲስ ለማድረግም እየተጋ ይገኛል።

መላው ሕዝባችን በአንድ በኩል አገራዊ ሰላምን በማወክ፤ በሽብርና ሁከት ስልጣን ለመያዝ የሚዳክረውን አሸባሪውን ትህነግና በአምሳሉ የፈጠራቸውን አሸባሪና ጽንፈኛ ኃይሎችን ቅዥት በመመከት ፤ በሌላ በኩል ቡድኑን እየጋለቡ ያሉ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን አገር የማፍረስ ሴራን በማክሸፍ ሉአላዊነቷ፣ አንድነቷ እና ሰላሟ የተጠበቀች አገርን ለማጽናት ቁርጠኛ ሆኖ እየታገለና ውድ ዋጋም እየከፈለ ይገኛል።

ይህ ስለ ሰላም ያለው ቁርጠኝነት አሸባሪዎችን በግንባር ፊት ለፊት በጀግንነት ከመፋለም ጀምሮ፤ አሸባሪዎች በየትኛውን አጋጣሚና ሁኔታ ተልዕኳቸውን መፈጸም የሚችሉባቸውን ዕድሎችና ክፍተቶች በመዝጋት ጭምር በተግባር እያሳየ ነው። ለዚህ ደግሞ በየቀኑ ከምንሰማቸው የአሸባሪዎች የሽብር እቅዶች ክሽፈት በስተጀርባ ያለውን የሕዝብ ተሳትፎ ማየት ብቻ በቂ ነው።

ሕዝቡ የሰላሙ ባለቤት የመሆኑን እውነታ ከመገንዘቡ የተነሳ ከጸጥታ ኃይሎች ጋር የፈጠረው ጥምረትና ጥምረቱ ይዞት የመጣው ስኬት ዛሬ ላይ ጠላቶቻችን እንዳሰቡት አገሪቱ የሁከትና የብጥብጥ ማዕከል እንዳትሆን አድርጓታል። ይልቁኑ ከሚርቶች በላይ የሆነ ሰላምና ልማት ባለቤት አድርጓታል።

ሕዝባችን የዕለት ተዕለት ሕይወቱን ከጸረ ሰላም ኃይሎች ከመጠበቅ ባለፈ በአደባባይ የሚከበሩ ብሔራዊ በዓላት በሰላም ተጀምረው በሰላም እንዲጠናቀቁ እያሳየ ያለው ተሳትፎም የዚሁ ለሰላም ያለው ቁርጠንነት ማሳያ ነው። እነዚህን በዓላት የአገራችን ጠላቶች የእኩይ ዓላማ ማስፈጸሚያ እንዳይሆኑ እያሳየ ያለው ትጋትም ለአገራዊ ሰላሙ አንድ ትልቅ አቅም ሆኗል።

አሸባሪዎች በዓላትን የእኩይ አላማቸው ማስፈጸሚያ እንዳያደርጉት በተለይ ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ሰላሙን ለመጠበቅ እያሳየ ያለው ንቁ ተሳትፎ ፤ ስለሰላም ያለውን ቀናኢነት ብቻ ሳይሆን የሰላም እሴቶቻችን በትውልዱ ውስጥ ሰፊ ስፍራ እንዳላቸው ያመላከተ ሆኗል።

ከዛም ባለፈ ዛሬም እንደመጣንባቸው ረጅም ዘመናት ሰላማችን በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ቢሆንም መጪው ዘመን የራሱ የሰላም ዜማ እንዳለው ፤ ለዚህ የሚሆን ትውልድ ስለመኖሩ ማረጋገጫም እየሰጠ ይገኛል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አሸባሪና ጽንፈኛ ቡድኖች በተለይ በአደባባይ የሚከበሩ ብሔራዊ በዓላትን የእኩይ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ለማድረግ ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ተስተውሏል። ይሁንና የጥፋት መሻታቸው በሕዝባችን ሰላም ወዳድነትና ከዚህ በሚመነጨው ሁለንተናዊ ተሳትፎ መምከን ችሏል።

ይህ ማለት ግን ስለጥፋት ተልዕኳቸው ስኬት በአላቱን መጠቀሚያ ላለማድረግ እጃቸውን አጣምረው ይቀመጣሉ ማለት አይደለም። ይህንን መቼም ቢሆን ሊያደርጉት አይችሉም ለዚህ የሚሆን ስብዕናም የላቸውምና ባገኙት አጋጣሚና ክፍተት ሁሉ ለተልዕኳቸው ስኬት አያንቀላፉም፤ ተኝተው አያድሩም።

የጠላቶቻችንን የጥፋት ህልም በቀጣይም ማምከን የምንችለው ስለሰላማችን ሁላችን እንደቀደሙት ጊዜያት ዘብ ስንቆም ብቻ ነው። ይህንንም በደመራ፣ በያሆዴ፣ በጊፋታ፣ በመስቀላ ዮ እና ሌሎች በዓላት በተጨባጭ አይተነዋል። በቀጣይም በትልቅ ድምቀት በሚከበረው በኢሬቻ በዓል በተጠናከረ መልኩ የምናየው ይሆናል።

የኛ ኢትዮጵያውያን በዓላቶቻችን መሠረት የሚደርጉት ከሁሉም በላይ ሰላምን ፤ ወንድማማችነት እና አብሮነትን እንጂ፤ ሁከትን ፣ ግጭት እና ብጥብጥን አይደለም። በዓላቱን ለዚህ እኩይ ተግባር መሣሪያ አድርጎ ለመጠቀም የሚደረግ የትኛውም ዓይነት ሙከራ ኢትዮጵያውያንን ከማንነታቸው ጋር የማጣላት ያህል ነው፤ ይህ ደግሞ ፈጽሞ ሊሳካ የሚችል አይደለም።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

# አሸባሪው ሕወሓትና የርሃብ ቁማሩ

**አሲ ሴሮ**

1977 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ፈታኝ ወቅት ነው:: ወቅቱ የሰሜኑ የአገራችን ክፍል በርሃብ የተጠቃበትና ሺዎች የረገፉበት ፤ ከርሃብ የተረፉትም ቀያቸውን ትተው እግር ወደ መራቸው የተሰደዱበት ወቅት ነው:: ኢትዮጵያም የዓለም መገናኛ ብዙኃን የወሬ ማድመቂያ ሆና የሰነበተችበትና ብዙኃንም እጃቸውን ለእርዳታ የዘረጉበት ጊዜ ነበር::

ይህ ክፉ ወቅት ግን ለአሸባሪው ሕወሓትና መሰሎቹ ግን የደስታ ጊዜ ነበር:: ከተራቡ አፎች እህል በመንጠቅ በርካታ ሚሊዮን ዶላሮችን አጋብሰዋል:: ለተራቡ ዜጎች ከዓለም ሕዝብ ከተሰበሰበው 100 ሚሊዮን ዶላር ውስጥ 95 ሚሊዮን ዶላሩን ለመሣሪያ ግዥ በማዋል ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል ሠርተዋል:: ሺዎች በየቀኑ እየረገፉ ባሉበት ወቅትም የየቡድኑ አባላት በደስታና በፌሽታ ዳንኪራ ሲወርዱ ተስተውለዋል::

የ1977 ዓ.ም ርሃብ በፈጠረላቸው መልካም አጋጣሚም እራሳቸውን በጦር መሣሪያ አደራጅተዋል:: የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ትኩረት ለማግኘት ችለዋል:: በዚህም ቀደም ካለው ጊዜ በተሻለ መልኩ በጦር ሜዳ ድል ቀንቷቸዋል:: ህልውናቸውንም በርሃብ ላይ አጽንተዋል:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕወሓት ርሃብና ድህነትን እንደዋነኛ በሥልጣን የመቆያ ስልት በመውሰድ የአገዛዙ አንዱ አካል አድርጎት ኖሯል::

አሸባሪው ሕወሓት ኢትዮጵያን ባስተዳደረባቸው 27 አመታት በአገሪቱ ልማትን ከማረጋገጥ ይልቅ የድሃ ድሃ በሚል መርጃ ግብር ሴፍትኔት ፕሮግራምን እንደዋነኛ የልማት መሣሪያ አድርጎ ሲያስተዳድር ቆይቷል:: አገሪቱ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶችና የሰው ኃይል ቢኖራትም ሕወሓት መራሹ አስተዳደር እነዚህን ሀብቶች በአግባቡ አስተባብሮ መምራት ባለመቻሉ ዜጎች ሴፍትኔት ጥገኛ እንዲሆኑ ተፈርዶባቸው ቆይቷል::

አሸባሪው ቡድን ቆሜለታለሁ ለሚለው የትግራይ ሕዝብ እንኳን ለውጥ ማምጣት አልፈለገም:: ትግራይን ሲስተዳድር በነበረበት ወቅትም 1ነጥብ 8 ሚሊዮን ሕዝብ በሴፍትኔት ይተዳደር ነበር:: ቡድን መራሹ አገዛዝ ሕዝብ በራሱ የተፈጥሮ ሀብትና እውቀት መጠቀም ከጀመረ ኋላቀር የሆነውን የኢህአዴግ አስተዳደር የመቀበል ፍላጎት ስለማይኖረው አደህይቶና አቆርቁዞ የመግዛት ስልትን ሲከተል ኖሯል:: በዚህም አገዛዙ በነበረባቸው የስልጣን አመታት የድህነት ምጣኔው ከፍተኛ ደረጃ ከመድረሱም በላይ በገንዘብ ሚኒስቴር መረጃ መሠረት ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከሚገኙ 50 አገራት በመበደር ተወዳዳሪ ያልተገኘላት አገር ለመሆን በቅታለች::

በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ማብቂያም የኢትዮጵያ የዕዳ መጠን ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርቷ እስከ 60 በመቶ የደረሰ በመሆኑ ኢትዮጵያ ከየትኛውም አገር ሆነ ተቋማት መበደር የማትችልበት ደረጃ ደርሳለች:: በዚህም በድህነቷ የዓለምን ትኩረት የሳበች አገር እንድሆን አድርጓታል:: ይህም ድህነትን እንደ አንድ ስኬት ለሚያየውና ኢትዮጵያን የማደህየትና የማቆርቆዝ አላማ ለነበረው የአሸባሪው ሕወሓት አስተዳደር እንደትልቅ ስኬት የሚታይ ነበር::

ድህነትንና ርሃብን እንደ አንድ የፖለቲካ መሣሪያ የሚጠቀመው ቡድን ከሥልጣን ተወግዶ መቀሌ ከመሸገ በኋላም የትግራይን ሕዝብ በማስራብ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል:: በተለይም ጥቅምት 20 ቀን 2013 በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት ከፈጸመ በኋላና በአፀፋውም ኢትዮጵያውያን በ15 ቀናት ውስጥ ቡድኑን ጠራርገው ተንቤን በርሃ ከከተቱት በኋላ በጦር ሜዳ ያጋጠመውን ሽንፈት በዲፕሎማሲ ለማሸነፍ በርካታ ሙከራዎችን አድርጓል::

ከእነዚህ ሙከራዎች ዋነኛው ደግሞ ትግራይ ሕዝብ ተርቧል የሚል የሀሰት ትርክት በማሰራጨት የውጭ ደጋፊዎቹና በእነሱ የሚታዘዙ መገናኛ ብዙኃን እንዲያስተጋቡለት ማድረግ አንዱ ስልት ነበር:: የኢትዮጵያ መንግሥት የመጀመሪያውን ዙር ጦርነት አገባዶ ከመቀሌ ሲወጣ ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ በመመደብ የትግራይ ሕዝብ እንዳይራብ በቂ የምግብ እህል ክምችትና የነዳጅና የመድኃኒት አቅርቦት በመጋዘኖች ውስጥ አስቀምጦ ወጥቷል::

ሆኖም ከሥልጣኑ ውጪ ለሕዝብ ሕይወት ደንታ የሌለው የሽብር ቡድኑ መንግሥት ትቶት የሄደውን የእርዳታ እህልና ነዳጅ ለጦር ኃይሉ ተጠቅሞበታል:: በምትኩም የትግራይ ሕዝብ ተራበ በማለት የቁራ ጩኸት ሲያሰማ ቆይቷል:: ይኸው ጩኸትም ዛሬም ድረስ ቀጥሏል:: መንግሥት በጦርነትም ውስጥ ሆኖ ለትግራይ ሕዝብ በማሰብ በርካታ የሰብአዊ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ቢሆንም ርሃብን እንደጦር መሣሪያ የመጠቀም ልምድ ያለው ይኸው አሸባሪ ቡድን የትግራይ ሕዝብ በርሃብ አለቀ የሚል የስላቅ ለቅሶ ሲያሰማ ቆይቷል::

በተለይም ይኸው ለቅሶው በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ ተአማኒነትን እንዲያገኝ የእርዳታ እህል ወደ ትግራይ እንዳይገባ በርካታ መሰናክሎችን ሲፈጥር ቆይቷል:: የእርዳታ እህል የጫኑ መኪኖች ወደ ትግራይ እንዳይገቡ ከማድረግ ጀምሮ የገቡትም እንዳይመሱ በማድረግ የጦር ኃይሉን ለማመላለሻነት እየተጠቀመበት ይገኛል::

እንደ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን መረጃ እስከ ነሐሴ ወር መጨረሻ ድረስም የእርዳታ እህል የጫኑ 6ሺ631 መኪኖች ወደ ትግራይ የገቡ ሲሆን መመለስ የቻሉት 4ሺ599 ብቻ ናቸው:: 2ሺ32 መኪኖች የአሸባሪ ቡድኑን ታጣቂዎች በማመላለስ ተግባራት ውስጥ ተጠምደው ይገኛሉ:: ይህ በእርዳታ አቅርቦቱ ላይ የራሱን አሉታዊ ጎን እንደሚያሳርፍ ቢታወቅም ርሃብን ዋነኛ የፖለቲካው መሣሪያ ማድረግ ለሚፈለግው አሸባሪው ሕወሓት ግን ከዚህም የከፋ እንዲመጣ ምኞቱ ነው::

«ለምጣዱ ሲባል አይጧ ትለፍ» እንደተባለውም መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ሲል አሸባሪ ቡድኑ እንደሚጠቀምበት እያወቀ በርካታ ሰብአዊ ዕርዳታዎችን ወደ ትግራይ ሲልክ ቆይቷል:: ከሐምሌ 1 ቀን 2014 እስከ ነሐሴ 3 ቀን 2014 ባለው አንድ ወር ውስጥ ብቻ ከ240 ሺ. በላይ ሜትሪክ ቶን ምግብ፤ 52ሺ. 645 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች፤ 258 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት፤ 7ሺ275 ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ እንዲሁም 2ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ወደ ትግራይ ተልኳል:: ይህ እንግዲህ አሸባሪ ቡድኑ ለጦርነት አቆብቁቦ በነበረባቸው ቀናት ዋዜማ ነው::

በትግራይ ሕዝብ ርሃብና ጉስቁልና ላይ ማትረፍና ዕድሜውን ማራዘም የሚፈልገው አሸባሪው ሕወሓት መንግሥት የላካቸው ሰብአዊ ዕርዳታዎች ወደ ኅብረተሰቡ እንዳይደርስ በማሰብ ከ547ሺ. ሊትር በላይ ነዳጅ ከተባበሩት መንግሥታት መጋዘን ውስጥ በመስረቅ የእርዳታ ማቅረቡን ሥራ አስተጓጉሏል::

የሽብር ቡድኑ መቀሌ ወደሚገኘው የድርጅቱ መጋዘን በኃይል በመግባት 12 የነዳጅ ቦቴዎችን በአጠቃላይ 570 ሺህ ሊትር ነዳጅ በዘረፈበት ወቅትም የዓለም ምግብ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዴቪድ ባስሌ የቡድኑ ድርጊት አሳፋሪና አስጸያፊ መሆኑን መግጻቸው የሚታወስ ነው::

አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለው ተግባር ከዚህም በላይ የሚያስብለው ቢሆንም ቡድኑ ዝርፊያ፤ ውንብድና ሌብነት እና ውሸት ያደገበት በመሆኑ አሳፋሪና አስጸያፊ ተግባራቱን ግብአተ መሬቱ እስኪፈጸም ድረስ የሚቀጥልበት ይመስላል:: ይህንን የትግራይ ሕዝብ በአግባቡ ተገንዝቦ ቡድኑን በቃህ ሊለው ይገባል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሲ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

# ባህላዊ ወረቶቻችንን ለብሔራዊ መግባባት

ወርሃ መስከረም በርካታ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓሎች የሚከወንበት ባለደማቅ ቀለማትና ህብራዊ ወር ነው። ተፈጥሮም ኢትዮጵያውያንም የሚያጌጡበት ሽቅርቅር ወር ነው። ባህላዊ ወረቶቻችን Cultural Capitals በርከት ብለው የሚገኙበት ባለጸጋ ወር ነው። ሆኖም በሌሎች ወራትም እንደ መስከረም ሁሉ ከፍ ያሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ወረቶች ቢኖሩም በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እየገለጥናቸው ፣ እየኖርናቸው፣ እየተረጎምናቸው እየወጣን እየገባንባቸው ስላልሆነ እና ላለፉት 50 አመታት ልዩነት ፣ ጥላቻ ፣ ጎሰኝነትና የፈጠራ ትርክት ተቋማዊና መዋቀራዊ ሆነው ስለተለፈፉ ፤ እዚህም እዚያም ቀውስ ፣ ነውር ለማመን የሚያስቸግሩ ጭካኔዎችን ፣ ግፎችን ፣ መከፋፈል ፣ መጠራጠር እያስተናገድን ነው።

ፈሪአ እግዚአብሔር አለው ከሚባለው የትግራይ ህዝብ አብራክ የወጣው አሸባሪው ሕወሓት ባለፉት 31 ዓመታት በተለይ ባለፉት አራት አመታት ከቡችሎቹና ተላላኪዎች ጋር በመቀናጀት የፈጸመውን ግፍና ጭካኔ አረመኔነት ለማየት እየዘገነነን ፣ ለመስማት እየሰቀጠጠን አብሮ ቢኖርም፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) የተቋቋመው የሚኒስትሮች ግብረ ኃይል ጥልቅ በሆነው ምርመራውና ጥናቱ የደረሰበትን ግኝት ይፋ ሲያደርግልን ደግሞ አዲስ ሆኖብናል። ተላላኪዎቹ ኦነግ_ሸኔ ፣ ቅማንት ፣ የጋምቤላ ፣ አገው ሸንጎና የጉሙዝ ታጣቂዎች የፈጸሟቸው ለማየት የሚዘገንኑ ለመስማት የሚሰቀጥጡ ኢ ሰብአዊ አረመኔያዊ ግፎችን ስንታዘብ የሶስቱ አብርሃማዊ ሃይማኖቶች ማለትም ክርስትና አይሁድና እስልምና በአንድነት በሚገኙበት ሀገር እንዴት ሊፈጸም ቻለ? ዋቄ ፈና የሚከተል ህዝብ ባለበት እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? ብለን ስንጠይቅ መልሱ ባህላዊ ወረቶቻችን በአግባቡ አልምተን ስላልተጠቀምንባቸው ነው።

ለመሆኑ ባህል ፣ ባህላዊ ንብረትስ ምንድን ነው የሚለውን ለመግባቢያ ያህል እንመለከት ። ባህል ሁሉንም የሚያስማማ የሚያግባባ ወጥ የሆነ ትርጉም ብያኔ ባይኖረውም የአንድ ማህብረሰብ ወይም ህዝብ እምነት ፣ ልማድ ፣ ወግ በኪነ ጥበብ እና በስነ ጥበብ ተዳውሮ ፣ ተሸምኖ ፣ ተንሰላስሎ የመገኘት ፣ የመገለጥ ዥጉርጉር ሕብራዊ ቀለም ነው። በደስታ ፣ በሀዘን ፣ በስራ ፣ በሃይማኖት ፣ በትምህርት ፣ ወዘተ . የህይወት ገጾች ይገለጻል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ባህልን፣ የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ ፣ ልማድ፣ እምነት፣ ...። በማለት ሲተረጉመው። የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በበኩሉ ባህል ፣ ልማድ ፣ ደንብ ሲል ይፈታዋል።

ባህላዊ ወረት (cultural capital) የሚለው ሀረግ ፔሬ ቦርዴው በተባለ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ የተነሳ የስነ ህብረተሰብ ተመራማሪ እንደተፈጠረ የተለያዩ የዘርፉ ድርሳናት ያትታሉ። ባህላዊ ወረት በማህበረሰብ ውስጥ ያለን ተቀባይነት ቦታ ከፍ ለማድረግ እውቀትን ፣ ፀባይና ክህሎትን የማሳደግ የማካበት ሂደት ነው። ባህላዊ ንብረት ወይም ወረት በግለሰብ ፣ በማህበረሰብ ከፍ ሲልም በህዝብ በሀገር ይሰላል። የበለፀገ ባህላዊ ንብረት ያካበተ ግለሰብ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ከፍ እንደሚያደርገው ሁሉ ያደገ የለማ ባህላዊ ንብረት ያለው ማህበረሰብ ህዝብ በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍ ያለ ተቀባይነት ይኖረዋል።

ባህል ማለትም የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ፣ ልማድ ፣ እምነት ፣ ወዘተ . በሂደት በእውቀትና በክህሎት እየበለፀገ ፣ እየዳበረ ሲሄድ ለሀገር ሰላም፣ አንድነት ከፍ ሲልም እድገት የላቀ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተቃራኒው ባህል በእውቀት፣ በክህሎት ካልበለፀገ አይደለም ለሀገር ሰላምና ዕድገት መዋል ይቅርና የማህበረሰቡን እሴቶች ጠብቆ ማቆየት ካለማስቻሉ ባሻገር የእለት ተእለት ችግሮችን እንኳ መፍታት የሚሳነው ይሆናል። ባህላዊ ንብረት እንደ ኢኮኖሚያዊ ንብረት ማለትም ገንዘብ በአግባቡ ኢንቨስት ተደርጎ ሰላምን ፣ ፍቅርን፣ እርቅን፣ መነጋገርን ፣ መቀባበልን ፣ መከባበርን ፣ መተባበርን ፣ አንድነትን ፣ ወዘተ... እውን ማድረግ ካልቻል እንደባከነ እንደከሰረ ሊቆጠር ይችላል።

ሀገርን ህዝብን ከግጭት ፣ ከቀውስ ፣ ከመፈናቀል፣ ከመጠራጠር ፣ ከጥላቻ ፣ ከበቀል፣ ወዘተ ... መታደግ አልቻለማ። እስኪ ለአንድ አፍታ ባህሎቻችንን እምነቶቻችንን ወይም ባህላዊ ንብረቶቻችንን ከዚህ አኳይ እንመዝናቸው። ባክነዋል ወይስ በአግባቡ ስራ ላይ ውለዋል ! ? አሁን ከምንገኝበት ሀገራዊ ቁመና አንጻር ባክነዋል ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል። ታዲያ እነዚህን ባህላዊ ንብረቶቻችንን እንደ ጦር እቃ ለብሶ እንደ ጥሩር ደፍቶ መውጣት መግባት ፣ መመላለስ ለምን ተሳነን? መልሱ ቀላል ነው። ላይ ላዩን እንከውናቸዋለን እንጂ አንኖራቸውም። በቃል እናነበንባቸዋለን እንጂ በልባችን አላተምናቸውም።በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እንሯሯጣለን እንጂ በስርዓተ ትምህርታችንን አካተን ትውልድን ለማነጽ አላዋልናቸውም። ለብሔራዊ መግባባት ፣ እርቅ ፣ አንድነትና ሰላም ካላቸው ፋይዳ ይልቅ ስለሚሰቡት ጎብኚና ቱሪስት እንጨነቃለን። ወደ ተራ ሸቀጥ እናወርዳቸዋለን። ይህ የተንሸዋረረ እይታ ሊስተካከል ይገባል።

“ባለንጀራህን ፣ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ” የሚሉ አብርሃማዊ እምነቶችን ማለትም ክርስትናን፣ እስልምናንና አይሁድን እየተከተልን እንዴት በጥል ግድግዳ ተለያየን!? በአንድ አምላክ በዋቄ ፈና እያመን ኢሬቻን በየአመቱ እያከበርን እየከወን ይቅር መባባል ለምን ተሳነን? መልሱን ለማግኘት ሚስጥሩን ለማወቅ ሞራ ማስገለጥ ወይም ኮከብ ማስቆጠር አያሻም። መልሱ ቀላል ነው። እሱም ባህላዊ ንብረቶቻችንን በካዝና ቆልፈን አስቀመጥን እንጂ ስራ ላይ ስላላዋልናቸው (ኢንቨስት) ስላላደረግናቸው ነው። ትልቁን የመደመር ፍልስፍናም ሆነ ሀገራዊ ሰላምና አንድነት እውን ለማድረግ የተቆለፈባቸውን ባህላዊ ንብረቶች ከካዝና አውጥቶ በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ በፍጥነት ማፍሰስ ኢንቨስት ማድረግ ይጠይቃል።

በኢኮኖሚክስ አስተምህሮ ባህል ከተፈጥሮ፣ ከሰውና ከአካላዊ ፣ ቁስ አካላዊ (physical) ቀጥሎ 4ኛው ንብረት ሆኖ መጠናት ፣ መተንተን ከጀመረ ከራርሟል። በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሀገር እድገትና ለዘላቂ ሰላም አስተዋጽኦ ያበረክታል። ሰላም በሌለበት ኢኮኖሚያዊ እድገትም ሆነ ብልፅግና ሊታሰብ አይችልምና። የመደመር ሶስቱን አላባውያን መሰብሰብ ፣ ማከማቸትና ማካበትን እውን ማድረግ አይታሰብም።

ለሀገር ግንባታ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ወሳኝ ሚና ከሚጫወተው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሥርዓት በተጨማሪ ለዘመናት እንደ ህዝብ ፣ እንደ ሀገር አጋምዶ ያቆየን ባህላዊ ንብረታችን ነው። ሁነቱን፣ ክዋኔውን፣ መንፈሱን ጠብቆ ተንከባክቦና አልምቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ፣ ማስቀጠል፣ ማክበርና ማስተዋወቅ ትልቅ ኃላፊነትም አደራም ነው። ሆኖም የመጨረሻ ግብ ሆኖ ግን ሊወሰድ አይገባም። ቱባነቱን እንደጠበቀ ማደግ ዘመንና ትውልድ መዋጀት ይጠበቅበታል። አዎ ! የትውልዱንና የዘመኑን ህፀፅ የሚያርም ለምፅ የሚያነጻ ፣ የሚዋጅና የሚቤዥ መሆን አለበት።

ዘረኝነትን ፣ ጥላቻን ፣ ቂም በቀልን ፣ ደባን ፣ መከፋፈልን ፣ ወዘተ ... መቤዥ ፣ መዋጀት አለበት።

ባህላዊ ንብረታችንን ይበልጥ በማጎልበት፣ በማልማትና በማስፋት ለመጻኢ እድላችን ፣ ለነገ ተስፋችን፣ ለእርቅ፣ ለሰላም ፣ ለአንድነት፣ ለሁለንተናዊ ብልፅግና፣ ለመደመር ወዘተ. ልናውለው ይገባል። ስኬቶቻችንን የምናወድስበት፣ ፈተናዎቻችንን የምንሻገርበት ነገአችንን የምንተልምበት ጭምር አድርጎ ስለመጠቀም አበክረን ማሰብ ያስፈልጋል።

የፍቅር ፣ የእርቅ ፣ የሰላም ፣ የአብሮነት ፣ የማካፈል፣ የመተባበር ፣ የመተጋገዝ ፣ የመረዳዳት፣ የምስጋና ፣ ወዘተ . ባህሎች ፣ ልማዶች ፣ እምነቶች፣ ሃይማኖቶች ከፍ ሲልም ድምር ባህላዊ ንብረቶች ባለቤት እንዲሁም የጥንታዊት ሀገር ባለቤት ሆነን አንድነትን በመከፋፈል ከሰዋን ፣ ፍቅር ከጎደለን፣ እርቅ ከገፋን ፣ ሰላም ከራቀን፣ አብሮነትን በቀዬአዊት ከተካን፣ ማካፈልን በስስት ከቀየርን ፣ መተባበርን በመለያየት ከለወጥን ፣ ምስጋናን በእርግማን ከተካን፣ ወዘተ ... ምኑን ሙሉኡ ሆነው? ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ያለፍንባቸው ሀገራዊ ውጣ ውረዶች፣ አሳፋሪ ድርጊቶች እውነት የእነዚህ ሁሉ መንፈሳዊና ባህላዊ ፀጋዎች ባለቤት ስለመሆናችን የሚመሰክሩ ናቸው? እስኪ ሌሎችን አቆይተን ካለፉት 19 ቀናት ወዲህ እንዲሁም ወደፊት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚከበሩ መንፈሳዊና ባህላዊ ሁነቶች የተሸከሙትን ግዙፍ መልዕክቶችና አንድምታዎች አለፍ አለፍ ብለን እየተመልከትን ሂሳብ እናወራርድ።

ፍቼ ጨምበለላ ፣ ቡሔ ፣ ሻደይ ፣ አሸንዳ፣ ሶለል አይነ ዋሬ ፣ እንቁጣጣሽ ፣ መስቀል ፣ መስቀላዮ፣ አጋመ፣ ጊፋታ ፣ ኢሬቻን ፣ ጋሮ ፣ ቺሜሪ ፣ ወዘተ ... በአንድም በሌላ በኩል በተለያዩ የሀገራችን ማህበረሰቦች የሚከበሩ ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ክዋኔዎች ናቸው። ሁሉም ማለት ይቻላል ተስፋን፣ ፍቅርን ፣ ነፃነትን ፣ አብሮነትን፣ ምስጋናን ፣ እርቅን፣ ይቅርታን ፣ ወዘተ . የሚያውጁ፣ የሚለፍፉ ናቸው። ግን በነቂስ ወጥተን ለዘመናት በየአመቱ በአደባባይ የምናከብራቸው የምንዘክራቸውን ያህል በዕለት ተዕለት ኑሮአችን አንኖራቸውም። አንለማመዳቸውም።

ከገጠሙን ቀውሶች ፣ ፈተናዎች መውጣት ማገገምና ማንሰራራት የቻልነው በቀሩን ሽርፍራፊ እንጥፍጣፊ በባህላዊ ንብረቶቻችን ነው ። በተለይ ባለፉት 27 ዓመታት ቀን ከሌት እንደ ተሰበከው ልዩነት ፣ ጥላቻና ዘረኝነት ቢሆን ኑሮ እርስ በእርስ ተበላልተናል። ተጨራርሰናል። ለዚህ ነው መዳኛችን፣ ማገገሚያችንና ማንሰራሪያችን የሆነውን ባህላዊ ንብረት ወደሙላቱ መመለስ ለነገ የሚባል ጉዳይ የማይሆነው። ባህላዊ ንብረታችን ለበጎ ዓላማ ሲውል ሀገርን ከጥፋት ከእልቂት እሳት እንደሚታደግ በጋሞ ሀገር ሽማግሌዎች ተመልክተናል።

ቁጣ አብራጁ ይህ የጋሞ አባቶች ልመና (ጋሞ ወጋ) እየጠፉ ፣ ትኩረት እየተነፈገው ያለው ባህላዊ ንብረታችን ተጠብቆ ለትውልድ ሲተላለፍ ሀገርን እንዴት ማዳን እንደሚችል ጥሩ ማሳያ ነው። የጋሞ አባቶች የ2011 ዓ.ም ልዩ የበጎ ሰው ተሸላሚ መሆናቸው በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለ አንዳች ልዩነት ዳር እስከዳር አድናቆትን ተቀባይነትን ያተረፈው በዚህ እሳቤ ነው።

ሰላምን ፣ ፍቅርን ፣ ይቅርታን ለማነፅ ፣ ለመገንባት ከምንሰጠው ትኩረት ባልተናነሰ በየአካባቢው እንደ ጋሞ ወጋ አይነት የሽምግልና ፣ የእርቅ ባህላዊ ካፒታሎቻችን ላይም መስራት ይጠበቅብናል። ከዚህ መሳ ለመሳ የአክራሪነት አዝማሚያ ፣ እኩይ አስተሳሰብ እንዲገታ ብሎም ተሸንፎ ከሰላምና ከእርቅ መንገድ ገለል ፣ ዘወር እንዲል ድልብ የሆኑ ባህላዊ ንብረቶቻችን ጥንስስ ፣ ወረት የማይተካ ሚና አላቸው። ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ባህላዊ ንብረቶች ባለፀጋ ስለሆኑ የየራሳቸውን መዋጮ ማበርከትና ወደ ስራ መግባት ይጠበቅባቸዋል።

በየአካባቢያችን ፣ በየቀዬአችን የምናንፀው፣ የምናቀነቅነው ከባቢያዊ ብሔርተኝነት ወደ አክራሪነት፣ ፅንፈኝነት የሚያንደረድር ወደገደል አፋፍ የሚገፋ ስለሆነ እነዚህን ባህላዊ ወረቶች በመጠቀም መግታት ያስፈልጋል። የዜጎች ማንነት እሴት እንደተከበረ ወደ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የሚያደርሰንን ቀና መንገድ በቅንነት መቀላቀል፣ መያያዝ ይገባል። ይህ ሀገራዊ ብሔርተኝነትም ከገደቡ ፣ ከውሃ ልኩ እንዳያልፍ ጥንቃቄ ማድረጉ እንዳለ ሆኖ ። አይደለም ዘውጌአዊ፣ ወንዜአዊ ብሔርተኝነት ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት በአግባቡ ካልተያዘ ፤ የጎረቤቱን የሚጎመጅ ፣ የሚመኝ፣ የሚመቀኝ ሆኖ የመውጣት አደጋ ስላለው በብልሀት፣ በማስተዋል ሊቃኝቃን ይገባል።

ባህላዊ ወረቶቻችን ለብሔራዊ እርቅ መግባባትና ሰላም ይዋሉ !!!

# ወቅታዊ

# “በአገር ውስጥ አንድነቱ የጠነከረ ሕዝብ በውጪ ተፅዕኖ ሰለባ የሚሆንበት ዕድል በጣም ጠባብ ነው”

*-የህግ ባለሙያ አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው*



ክፍለዮሐንስ አንበርብር

በሥራ ዓለም ሳለፉት 15 ዓመታት በህግ ሙያ ያገለገሉ ሲሆን በቀድሞ ፍትህ ሚኒስቴር በተለያዩ የስራ ደረጃዎች ላይ ሠርተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ጠበቃና የህግ አማካሪ ሆነው ሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ በማህበር አመራርነት በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማህበር በሥራ አስፈፃሚነት እና የህትመትና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፤ በተለያዩ የቦርድ መዋቅሮች አባልና አማካሪ ሆነው ይሰራሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 1249/2013 የተቋቋመው የኢትዮጵያ የፌደራል ጠበቆች ማህበርን በምክትል ፕሬዚዳንትነት እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው የትምህርት ዝግጅታቸው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በህግ የወሰዱ ሲሆን ማስተርስ ዲግሪያቸውን በዓለም አቀፍ ህግ ወስደዋል፡፡ እንዲሁም በፌደራል ስተዲስ የትምህርት ዘርፍ ተጨማሪ የማስተርስ ዲግሪ እ.ኤ.አ በ2013 ተቀብለዋል፡፡ በዛሬው ዕትማችን የዝግጅት ክፍላችን እንግዳ አድርገናቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሰሞኑን የተለያዩ ዓለም አቀፍ የተባበሩት መንግስታት፣ የዓለም ጤና ድርጅት እና ሌሎችንም ተቋማት ኢትዮጵያን በተመለከተ ብዙ መግለጫዎችን እያወጡ ነው:: በፌዴራል መንግስት እና በአሸባሪው ትህነግ ኃይሎች መካከል ያለውን ግጭት በሚመለከት ገለልተኛ መሆን ሲገባቸው ለአንዱ ያጋደለ መግለጫ ይሰጣሉ:: ይህንን እርሶ በህግ ዓይን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** እንግዲህ ባለፉት ሁለት ዓመታት በተደጋጋሚ ስንናገር እና ስናስገነዝብ እንደነበረው እነዚህ ዓለም አቀፍ ተቋማት ከጅምሩ ሲቋቋሙ የተቋቋሙበት ዓላማ አላቸው:: እንዲያሳኩ የተፈለጉባቸው ግቦች አሏቸው:: ያ ግብ በተባበሩት መንግስታት መቋቋሚያ ቻርተር እንዲሁም በተለያዩ የኤጀንሲዎቻቸው ሰነዶች ላይ የዓለም አገሮች ተስማምተውባቸው ፈርመውባቸዋል:: ስለዚህ በዛ ደረጃ የተቋቋሙበትን ዓላማ እንዲያሳኩ ይጠበቃል::

አሁን በጥያቄው ላይ እንደተነሳው ባለፉት ሁለት ዓመታት የነበሩት ነገሮች የእነዚህን ተቋማት ቀጣይ ዕጣ ፈንታም ጭምር ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው:: በረዥም ጊዜ ተዓማኒነት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ የሚችል ነው:: ተዓማኒነታቸው ጥያቄ ውስጥ እንዲገባም ያደርጋል:: ለማሳያ በተደጋጋሚ የገለፅነው ነው:: ምዕራባውያኑ በተደጋጋሚ እነዚህን ተቋማት በተለያየ መንገድ ተፅዕኖ ስር ይከቷቸዋል:: ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ብንመለከት ከዓመታዊ በጀቱ እስከ 30 በመቶ በአንድ አገር የሚሸፈን ነው:: እንደተለመደው ከበጀት ጀምሮ በተፅዕኖ ውስጥ የሚወድቁ ናቸው:: በዳይሬክተር ጄኔራል ደረጃም ሆነ በሴክሬተሪ ደረጃ የሚመጡት ሰዎች ብዙ ጊዜ እነርሱን ከሚቃረን አገር አይደሉም :: ስለዚህ ተቋማቱ አሁን አሁን እያገለገሉ ያሉት በተቋቋሙበት ዓላማ ሳይሆን የአንድን አካል ወይም ቡድን ይረዳል ተብሎ በሚታሰብ መንገድ ነገሮችን ሁሉ ወደሚፈልጉት የመውሰድ ዝንባሌና ሁኔታ ይታያል::

ይህ ደግሞ የሚጠቅም አይደለም:: ቀድሞም በአቋማቸው የተለዩ አገራት መሪዎቻቸውን ሰይጣናዊ ስዕል በመስጠት ያገሉታል:: ከዚያ በኋላ በሚዲያ ተቋሞቻቸው ተከታታይ ጥቃት ይከፍታሉ:: እዚህ ላይ የኢራቁን መሪ ሳዳም ሁሴንን ማንሳት ይቻላል:: በዚያን ጊዜ የመረጃው ልውውጥ በዚህ ልክ ስላልነበር እና ዓለም የነበረችበት ሁኔታ እውነታቸውን ለማስረዳት የሚችሉበትን ዕድል አለማግኘታቸው እንጂ ሁኔታው

> **በአንድ ቡድን እና በፌዴራል መንግስት መካከል ያለ ግጭት ይመስላል፡፡ ነገር ግን ይህ በተግባር ከዚያ በላይ ነው፡፡ በተግባር እዚህ ላይ እጃቸውን እያስገቡ ያሉ አካላት በጣም ብዙ ናቸው፡፡ ሁሉም ጥቅም አላቸው፡፡ ስለዚህ ጥቅማቸውን ለማስከበር ለሚያደርጉት ሁኔታ ይህ እንደ አንድ አጋጣሚ ተወስዷል፡፡ ይሄ ከኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ከወጣ በጣም ቆይቷል**

ብዙ መልዕክት የሚሰጥ ነበር:: የአሁኑም የዚያ ቀጣይ ክፍል ነው እየሆነ ያለው፤ ምዕራባውያን ብቻ ሳይሆን ሚዲያዎቻቸው እነ ኒዎርክ ታይምስ፣ ሲኤን ኤን፣ ቢቢሲ፣ አንዳንዴም አልጄዚራም አንዳንዴ የጋራ ጥቅም ሲኖራቸው የተናበበ ሥራ ይሠራሉ:: አሁን እየሆነ ያለው ይህ ነው፤ ግን ተገቢ አይደለም:: ከዓለም ዓቀፍ ህጎችም ሆነ ደንቦች ጋር ይቃረናል:: ከዛ ባለፈ በእኔ እምነት ችግሩ ኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ላይ ነው:: ይህ ደግሞ የአገራትን ግንኙነት የሚረብሽ ሲሆን፤ እርስ በእርስ መተማመን እንዳይኖር የሚያደርግ እና ለሚሠሩትም እንቅፋት የሚሆን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ከሩቁ ከሳዳም በተጨማሪ የሲቢያ ጉዳይ አይረሳም:: ሌሎች አገራት ሳይም በተመሳሳይ መልኩ ተደርጓል:: በአብዛኛው አፍሪካ ላይ የሰብዓዊ መብት አይከበርም እያሉ ጫና ይፈጥራሉ:: በተቃራኒው በዚያው በእነርሱ ሀገር ጥቁሮች ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ይፈፀማል:: እነዚህ ዓለም አቀፍ ተቋማት ሰብዓዊ መብት አፍሪካ ላይ ብቻ መከበር አለበት ከሚሉ ዓለም አቀፍ ህግ በእነርሱም ሀገር መጣሱ €€ተገቢ አይደለም« ለምን አይሉም ?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** እንግዲህ ጉዳዩን በተመሳሳይ ሚዛን መዳኘት ባለመኖሩ ተቋማቱ ጥያቄ ውስጥ እንዲገቡ እያደረጋቸው ነው:: ራሳቸው ምዕራባውያኑ በተለያዩ ሀገራት ሲፈፅሟቸው የነበሩ ነገሮች አሉ:: በአጋሮቻቸው አማካኝነት በየሀገሩ ከፖለቲካ ሁኔታዎቻቸው አንፃር ሊከሰቱ የሚችሉ ነገሮች አሉ:: እነዚያን ነገሮች እኩል አለማስተናገዳቸው ተዓማኒነት ያሳጣቸዋል:: አንድን ነገር ገንብተው በዚያው ልክ መንቀሳቀስ ሲጠበቅባቸው፤ መሬት ላይ የሌለን ነገር በማምጣት ጣልቃ ለመግባት እንዲያገለግል ያደርጋሉ:: ለምሳሌ ኒውክሌር በሌለበት ሀገር ልክ ኒውክሌር እንዳለ አድርገው በትልልቆቹ ሚዲያዎቻቸው በማስተጋባትና በቀላሉ ተፅዕኖ በመፍጠር ዓላማቸውን ያሳካሉ:: ሆኖም በመጨረሻ ያሉት ነገር እውነት ሆኖ አይገኝም::

አሁንም እንደምናየው እነራሺያ፣ቻይና እና ብራዚል በተወሰነ መልክ ከላቲን አሜሪካ የተለየ አማራጭ የመፈለግ ሂደት ውስጥ ከገቡ ቆይተዋል:: ባለፉት 20 እና 30 ዓመታት እነዚህ ነገሮች የበለጠ እየጎሉ መጥተዋል:: አሁን ደግሞ በየቀጣናው ያሉ ጉዳዮችም በዝተዋል:: የራሺያ እና የዩክሬን ጉዳይ አለ:: እዚህ የአፍሪካ ቀንድ ላይ የኢትዮጵያ ጉዳይ ትልቅ ነው:: ሌላው ቀደም ብሎ እነርሱ በጊዜ ያጠናቀቁት የሊቢያ ጉዳይ አለ:: የመን አካባቢም የመካከለኛው ምስራቅ ጉዳይ አለ:: ሁሉም እነርሱ በሚያስቡበት ደረጃ እስካልተገኙ ድረስ የውስጥ ሰላም አይኖራቸውም:: ስለዚህ ማሳያዎቹ ብዙ ናቸው:: ከእኛ ጋር ነህ ያለበለዚያ የእኛ ጠላት ነህ የሚሉ ናቸው:: የራስ መንገድ ብሎ ነገር የለም:: ሁሉም ነገር በእኛ ቡራኬ መሆን አለበት የሚል የቆየ አስተሳሰብ አላቸው:: እንዲያውም አሁን እየተፈተነ እየቀነሰ መጣ እንጂ፤ ለረዥም ጊዜ ከዚህም በከፋ መልኩ ሲፈፀም ነበር:: ይህ ደግሞ ከቅኝ ግዛት ጀምሮ በደንብ መሰረት የነበረው እና ስር የያዘ ነው:: አፍሪካውያኖችን እንደሰው ካለመቁጠር አስተሳሰብ የመጣ ውልደት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት፤ ግብፅ በሲናይ በርሃ፣ ጎረቤት ሱዳንንም ወታደራዊ መንግስት መጥቶ ስልጣን እስከመያዝ የደረሰ ቀውስ እያስተናገደች ነው:: ሆኖም ምዕራባውያን የወታደራዊ መንግስት አይፈልጉም ተብሎ ይታሰባል:: ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ደግሞ አንድ ቡድን ከመንግስት ጋር በመጋጨቱ ተደጋጋሚ ስብሰባዎችን ለማካሔድ የተገፋፉትና የኢትዮጵያን ጉዳይ አጥብቀው የያዙት ለምንድን ነው?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ኢትዮጵያ ጠቃሚ ሀገር ናት:: እኛ ሀገሪቱን የያዝንበት መንገድ እና በተለያዩ ጊዜያት የነበሩት መንግስታት ሀገሪቱን የያዙበት መንገድ ምንም ሆነ ምን ያለንን አቅም ተጠቅመን ኢትዮጵያን እንደ ትልቅነቷ ትልቅ ለማድረግ እየሰራን ነው ወይ የሚለው ጥያቄ እንዳለ ቢሆንም በጣም ትልቅ ሀገር ናት:: አፍሪካ ውስጥ እንደምሳሌ ሊጠቅሷት የምትችል ሀገር ናት:: ፖለቲካሊ፤ ጂኦ ፖለቲክሱም በጣም ቁልፍ ከሆነው

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ቀይ ባህር አጠገብ የምትገኝ ትልቋ ሀገር ናት:: 120 ሚሊየን የሚገመት ሕዝብ ያላት ሀገር ናት::

የባብዔል መንደብ እና በጣም ቁልፍ የሚባሉ ስትራቴጂክ ቦታዎች የእዚሁ አገር ቅርብ ናቸው:: ያለንበት ቦታም ጭምር ጠቃሚ እና ተሰሚነታችንን ከፍ የሚያደርግ ነው:: ኢትዮጵያ በጣም ጠቃሚ ናት:: ከቅኝ ግዛት ጀምሮ ለብዙ አፍሪካ ሀገራት እንደምሳሌ የምትታይ ናት:: ከአፍሪካ ህብረት መመስረት ጀምሮ በጣም ቁልፍ ሚና ያላት ቁልፍ ሀገር ናት:: አሁንም የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫ ከመሆኗ በተጨማሪ የአፍሪካ ሀገራትን ማስቀጠል የምትችል ሀገር ናት:: እንዲሁ ዝም ብሎ እንደ አንድ ሀገር ብቻ መቆጣር የምትችል አይደለችም:: ስለዚህ ጉዳዩ የተለየ የሚሆነው በዚህ ነው:: እንዳልከውም በአንድ ቡድን እና በፌዴራል መንግስት መካከል ያለ ግጭት ይመስላል:: ነገር ግን ይህ በተግባር ከዚያ በላይ ነው:: በተግባር እዚህ ላይ እጃቸውን እያስገቡ ያሉ አካላት በጣም ብዙ ናቸው:: ሁሉም ጥቅም አላቸው:: ስለዚህ ጥቅማቸውን ለማስከበር ለሚያደርጉት ሁኔታ ይህ እንደ አንድ አጋጣሚ ተወስዷል:: ይሄ ከኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ከወጣ በጣም ቆይቷል::

**አዲስ ዘመን፡- ጉዳዩ የፌዴራል መንግስት እና የአንድ ቡድን ወይም የአንድ ክልል ጉዳይ ይምሰል እንጂ ከበስተጀርባው ብዙ ኃይሎች መኖራቸው እርሶም እየገለጹ ነው:: በዚህ ወቅት አልሸባብ ጥቃት ለመሰንዘር ሞክሯል:: ሌሎች የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችም በተለያዩ መልኩ በውስጥም በውጪም እጃቸውን ጣልቃ እያስገቡ ናቸው። ከአፍሪካ ሕብረት ቻርተሮች አንዱ በሌላ ሀገር ውስጥ ጣልቃ አለመግባት ነው። ይሄ እየተጣሰ ይመስላል፤ ለምን ሆነ?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ትክክል ነው:: ስለውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እና ስለ ሉዓዋላዊነት ስናወራ ሁልጊዜም ቢሆን በተለይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሚሰራው ከውስጥ ወደ ውጪ ነው:: ለውጪ የሚታየው ማንኛውም ነገር የውስጥ ጥንካሬን ያሳያል:: ስለዚህ በእነዚህ አካላት ግምገማ ምናልባት ኢትዮጵያ በውስጥ ጉዳይዋ ተዳክማለች የሚል ግምገማ ስላላቸው ፍላጎቶቻቸውን ለማስጠበቅ ይህ ምቹ ወቅት ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ:: የራሳቸው ቀመር ይኖራቸዋል:: የውስጥ ጉዳያችንን ማጠናከር የእኛ እና ስልጣን የያዘው መንግስት ጉዳይ እንጂ የማንም ጉዳይ አይደለም:: በውስጥ ጉዳይ የተዳከመ ሀገር በማናቸውም ሁኔታ በቀጣናውም ሆነ በክልሉ እንዲሁም በዓለም ላይም ጠንክሮ ሊወጣ አይችልም:: ስለዚህ የውስጥ አንድነቱን ያላስጠበቀ አገር መፈተኑ አይቀርም::

የተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀፅ አንድ እና ሁለት ሲታይ መጀመሪያ መሰረት የሚያደርገው ሉዓላዊነት ነው:: ስለዚህ ሀገሮች ወደ ዓለም አቀፋዊ ግዴታ ሲመጡ ሉዓላዊነታችን ተጠብቆ ነው:: ስለዚህ አንዱ ሀገር በሌላው ሀገር ሀብታም ወይም ጠንካራ ሀገር በድሃ ወይም በደካማ ሀገር ላይ ጣልቃ አይገባም በሚል እሳቤ ነው:: ስለዚህ እየተደረገ ያለው ነገር ከተባበሩት መንግስታት ቻርተርም ሆነ ሀገራት ከሚገዙበት መርህ እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ አንፃር ልማዶች ደንቦች አንፃር ሲታይ ትክክል አይደለም:: ነገር ግን ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት የውጭ ጉዳይ ጥንካሬ መሰረት የሚያደርገው የውስጥ ጥንካሬ ነው:: የህዝቦች አንድነትን ማስጠበቅ መቻል ይገባል:: በውስጥ ያለው ሶሾ- ኢኮኖሚክ ጉዳዮች በሙሉ ተጋግዘው የውስጥ ጉዳይ በዚያ መልኩ የተሳለጠ ሲሆን በውስጥ ያለው የፖለቲካ ሥርዓትም ሆነ ሶሾ- ኢኮኖሚክ ጉዳዮች በሙሉ ተጋግዘው ካልሔዱ የራሳቸውን ጫና ይፈጥራሉ::

ሁለተኛ መታወቅ ያለበት እዚህ ቀጣና ላይ ሁሉም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆኖ መውጣት ይፈልጋል:: በተለይ ኢትዮጵያ እና ኬኒያ በግልፅ ይህ ፍላጎት እንዳላቸው ያለፉት ዓመታት ልምዳቸው ያሳያል:: ስለዚህ እንደዚህ ያሉ አጋጣሚዎች ላይ ራሳቸውን የተሻሉ አድርጎ ማቅረብ ይፈልጋሉ:: ይህ የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ክፍል ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያን ከሚቃረኑ ሀራት በስተጀርባስ የቅኝ ገዢዎች ፍላጎት የለም?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ይህማ የታወቀ ነው:: እንደ



ኢትዮጵያ ለውጪ መንግስታት ተፅዕኖ አንበረከክም ብለው የቆዩ አይደሉም:: ታሪካቸውም ሲታይ በተለይ እኛ አካባቢ ያሉት የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሀገሮች ናቸው:: የእንግሊዝ ቅኝ ተገዢዎች ተብለው አሁንም ድረስ ኢኮኖሚያቸውም ሆነ ሌላ ሌላውም በብዙ መልኩ ጣልቃ የተገባባቸው ናቸው:: ስለዚህ የቅኝ ገዢዎች ተፅዕኖ ውስጥ መግባታቸው እና ዓላማቸውንም መቀበላቸው የሚጠበቅ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በሀገራት የውስጥ ጉዳይ ሳይ ገለልተኛ አለመሆን ሲባል በተባበሩት መንግስታት ኢትዮጵያ ጉዳያቸው ሆና በጎረቤት ሀገራት ጭምር ተፅዕኖ ውስጥ እንዳትወድቅ ምን ማድረግ አለበት? ኢትዮጵያ በውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች አጣብቂኝ ውስጥ እንድትገባ ምን ታድርግ?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ደጋግመን ስናወሳ እንደነበረው ነገር ይህም በተመሳሳይ ከላይ ካልኩት ጋር ይያያዛል:: በዓለም አቀፍ ጉዳይ ላይ ጠንካራ ሆኖ መውጣት የሚቻለው የውስጥ አንድነትን ማስጠበቅ ሲቻል ነው:: ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ሲኖር ነው:: የህዝቦች አንድነት መጠናከር መሠረታዊ ነው:: ስለዚህ በአገር ውስጥ አንድነቱ የጠነከረ ሕዝብ በውጪ ተፅዕኖ የሚወድቅበት እና ሰለባ የሚሆንበት ዕድል በጣም ጠባብ ነው:: ተፅዕኖ ቢመጣ እንኳን መቋቋም ይቻላል:: አሁን እነራሺያ ይህንን ተፅዕኖ ይዘው ቆይተዋል:: በእርግጥ ጉልበት ባገኙ ሰዓት በቻሉት መጠን አፈራርሰዋቸዋል:: ግን አሁንም የውስጥ አንድነታቸውን ማስጠበቅ በመቻላቸው፤ ኢኮኖሚያቸውን አሁን ያለበት ደረጃ አድርሰው አሁን ደግሞ በጣም በተሻለ ደረጃ ላይ ሆነው የእነርሱን ጥቅሞች ወደ ማጥቃት ተሸጋግረዋል:: ስለዚህ ከምንም በላይ ሀገሮች የውስጥ ጉዳያቸው በጣም አስፈላጊና መሠረታዊ ነው::

ከዚህ ባለፈ በዲፕሎማሲ ላይ በጣም በርካታ ሥራዎች አሉ:: በህዝቦች መካከል አለመተማመን እና ብዙ ሽንቁር ካለ፤ በቡድኖች መካከል ያልተመለሱ ጥያቄዎችና ስልጣን ላይ ያለው መንግስት የኔ መንግስት አይደለም የሚል የህዝብ ክፍል ካለ ይህን ይዞ ወደ ዓለም አቀፍ መድረክ መውጣት በጣም ከባድ ነው:: ስለዚህ ይህንን ካረጋገጥን በዲፕሎማሲ በኩልም መሰራት ያለባቸው ሥራዎች አሉ:: በኢትዮጵያ ከሞላ ጎደል ልምድ ያላቸው ዲፕሎማቶች አሏት:: መግለጫ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በየሀገሩ ያሉ ዲፕሎማቶቻችን በተለይ ከዚህ ግጭት ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያን እውነት ማሳየት ይኖርባቸዋል::

ኢትዮጵያ ላይ የሚወጡት ሪፖርቶች በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም:: ሀገርን የሚጠቅም እና ትክክለኛ ሪፖርት ቢሆን ኖሮ እኛም በይፋ እንደግፈው ነበር:: የግድ አሜሪካ ስላለችው መቃወማችን አይደለም:: ነገር ግን የያዙት አቋም በግልፅ በሚያስታውቅ መልኩ ሚዛን የጎደለው እና ከእውነት የራቀ፤ የኢትዮጵያን እና የህዝቦቿን ጥቅም ከፍ ባለ ደረጃ ሊጎዳ የሚችል በመሆኑ ነው:: ማንኛውም ሀገር ጥቅሙን የሚያረጋግጠው ኢትዮጵያን ዋጋ አስከፍሎ መሆን የለበትም:: የእነርሱ ጥቅም ከኢትጵያ እና ከህዝቦቿ ጋር አብሮ የሚሔድ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ካለው በተጨማሪ ዲፕሎማሲው ላይ መሠራት አለበት እያሉ ነው?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** አዎ! ዲፕሎማሲው ላይ ብዙ መሠራት አለበት:: ተከታታይ ማስተባበያዎች መስጠታቸው ተገቢ ነው:: እነዚያን የበለጠ ተጨባጭ ማድረግ ተገቢ ነው:: በውስጥ ያለ ነገርም የውጪው አካል ጋር ሳይደርስ ቶሎ መፍታት አስፈላጊ ነው::

**አዲስ ዘመን፡-ምዕራባውያን የሚያወጧቸው መግለጫዎች የፌዴራል መንግስት ላይ ብቻ ያነጣጠሩ ናቸው:: ለአንድ ወገን ያደላ መሆኑ ተቀባይነቱን አያሳጣው? ሰሞኑን ራሳቸው ባወጡት ሪፖርትም ትግራይ ክልል መሔድ እንዳልቻሉ ገልፀው፤ ነገር ግን ይህን ያህል መድሃኒት እና ሌሎችም ወደ ትግራይ ያልገቡ ዕርዳታዎች አሉ ብለዋል:: ይህ ተዓማኒነቱን እና ቅቡልነቱን አያሳጣውም?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** አሁን ብቻ አይደለም:: ባለፉት ሁለት ዓመታትም ዝንባሌያቸው ተመሳሳይ ነው:: አንድ ጥናት እውነተኛ ጥናት ለመባል በትንሹ ማሟላት ያለበት መለኪያ መስፈርት አለ:: አንደኛው የመረጃ አሰባሰብ መንገድ ነው:: ሁለተኛው የመረጃው ምንጭ ነው::

ትንታኔው ሁሉንም አካል ያካተተ ነው ወይ የሚለው ሲታይ፤ የአሁኑ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊትም የነበሩት ተመሳሳይ ናቸው:: ለምሳሌ ጥቃት ደርሷል አልደረሰም የሚለውን ያረጋገጡት በስልክ ጠይቀው ነው:: ይህ በጣም ጥናቱን የሚያወርደው ነው:: ለምሳሌ እኔ ማንኛውንም ሰው አቅርቤ የፈለገውን እንዲል ላደርግ እችላለሁ:: ስለዚህ ምንጩ በእርግጠኝነት ተዓማኒ ካልሆነ የመጨረሻ ግኝቱም ተዓማኒ አይሆንም:: አጥኚዎቹ በአካል እንዲገኙ ይመከራል:: ከመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ጀምሮ ሁለቱንም ወገን አሳትፏል ወይ የሚለው ይታያል:: አንድ ጥናት ተቀባይነት አለው የለውም ለማለት እነዚህ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው:: ምክንያቱም መደምደሚያ ላይ የሚደረሰው ምንጩን መሠረት በማድረግ ነው::

ሌላኛው ደግሞ እኔን ትኩረቴን የሚስቡት ነገሮች ጥናቶች የሚወጡበት ጊዜ ነው:: ለምሳሌ ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት አመንስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት ብሎ ያወጣው የተናጥል ተኩስ አቁም ተደርጎ፤ ሰራዊቱ ከትግራይ ወጥቶ በዝምታ ወራቶች ሲያልፉ ነበር:: ልክ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ማጥቃት እና ቦታዎችን መያዝ ሲጀምር ሪፖርቱ ወጣ:: ሪፖርቱ የሚወጣበት ሰዓትም የተሰላ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ጦርነቱ በቆመበት ሰዓት መውጣት አይችልም ነበር?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** በእርግጥ አዎ! ግን ሪፖርት የሚያወጡት ጫና መፍጠር ሲፈለግ ይመስላል:: ይህ ጠቃሚ አይደለም:: የተቋማቱን ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ ይከታል:: በሥራቸው ከ200 በላይ አገሮች አሉ:: ይህ ዓለም ሰፊ ነው:: ወደ ፊት ከዚህ በላይ የሰፉ ነገሮች ሊያጋጥሙ እና እነዚህ ተቋማት የሚያስፈልጉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: ያንን የወደፊት ችግር እንዳይፈቱ፤ የሀገሮች ግንኙነትም በጣም በተካረረ መልኩ እንዲቀጥል እያደረገ ያለ በጣም አደገኛ ነው:: ውጤቱ ከኢትዮጵያም አልፎ ሌላም ችግር አለው::

**አዲስ ዘመን፡- መግለጫዎቹ ሲታዩ የኢትዮጵያ መንግስት እና የትግራይ መንግስት እያሉ ነው:: አሸባሪ ናቸው ተብለው በህዝብ እንደራሴዎች ውሳኔ የተላለፈ ቢሆንም እነርሱ ግን ግንኙነት እስከመመስረት ሄደዋል:: ለምሳሌ ሶማሊያ ቢኬድ ከአልሸባብ ጋር ግንኙነት አይመሰርቱም ወይንም አይወዳጁም:: ሌሎች ከቦኮሃራም ጋርም ግንኙነት አይመሰርቱም:: በኢትዮጵያ በኩል ያለውን አሸባሪ ግን እንደ ትግራይ መንግስት እያቀረቡ ነው:: እዚህ ላይ መንግስት ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት አለበት?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ይህንን በተከታታይ መግለጫዎች ማፍረስ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም የአገር ሉዓዓላዊነት ከሁሉም በላይ ነው:: ሉዓላዊነት ማለት ማዕከላዊ መንግስቱን ያዋቀረውን ማክበር ማለት ነው:: ኢትዮጵያ የምትመራው በሕገ-መንግስቱ መሠረት በማዕከላዊ መንግስት ነው:: ማዕከላዊ መንግስት በማያውቅበት ሁኔታ ከክልሎች ጋርም ሆነ ከማንኛውም ቡድን ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚፈቀድ አይደለም:: ሌሎች ሀገራትም ይህ ነገር እንዲፈፀም አያደርጉም:: ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዳበረ መርህ ነው፤ ይህን መጣስ ተገቢ አይደለም:: በተከታታይ ያንን ማረም ነው:: ይህ ሲሆን ከማዕከላዊ መንግስት በጣም አፋጣኝ እና ግልፅ አቋም ይዞ መኮነን ያስፈልጋል:: በዚህ ላይ ቀይ መስመር መኖር አለበት:: አሜሪካ ከአልሸባብ ጋር ብዙ ጊዜ ተነጋግራለች:: መነጋገር ይኖራል:: ነገር ግን በዲፕሎማሲ የሚኬድባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ:: በዛው መልክ ሊኬድበት ይችላል::

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ተቋማት ልክ ኢራቅ እና ሌሎች ሀገራትን ከወደሙ በኋላ የወረርነው በስህተት ነው እንዳሉት ሁሉ፤ ኢትዮጵያ ሳይ ለፈጠሩት ያልተገባ ጫና ይቅርታ የመጠየቅ ዕድል ይኖራቸዋል::**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ይህ እንደሁኔታው ነው:: ጊዜው ይወስነዋል:: አሜሪካኖቹ ሕወሓት በስልጣን ላይ በነበረበት ዘመን በተለይ ወደ መጨረሻ አካባቢ ደስተኞች አልነበሩም:: ስለዚህ ወቅቱ ይወስነዋል:: ጦርነቱ ሲጀመር የነበራቸው አቋም እና ከቆይታ በኋላ የነበራቸው አቋም የተለያየ ነው:: ግራና ቀኝ ያሉት ተዋናይ ተመሳሳይ ሆነውም እንኳን ራሳቸው በመቀያየራቸው ራሱ ራሳቸው ጋር ያለው አቋም ይቀያየራል:: እኔ በዓለም አቀፍ ደረጃ ላለው ህግ መከበር፤ ለዓለም አቀፍ ህጎች ደንቦች ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገር ከተፈለገ ይህ ስህተት እንደሆነ በይፋ መታመን አለበት:: ምክንያቱም ብዙ መታለፍ የሌለባቸውን መስመሮች ታልፈዋል:: ይህ እኛ ኢትዮጵያዊ ስለሆንን ሳይሆን ለብዙ ሀገሮች መጥፎ ዝንባሌ ሆኖ የሚቀጥል በመሆኑ ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል እላለሁ:: የቀድሞውና የአሁኑ ፕሬዚዳንቶች የነበራቸው አቋም ይለያያል:: ከፓርቲ እና ከሌሎችም ብዙ ነገሮች አንፃር የተለያየ ስለሆነ ቀድሞ መናገር ይቸግራል::

**አዲስ ዘመን፡- የእረፍት ጊዜዎን በመሻማቴ ይቅርታ እየጠየኩ ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ሥም አመሰግናለሁ::**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ምንም አይደል፤እኔም አመሰግናለሁ::

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ከውድመት አገግሞ በፍጥነት ወደ ሥራ የተመለሰው ኢንዱስትሪ ፓርክ

አንተነህ ቸሬ



**የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ማምረት ሥራው ከተመለሰ በኋላ ሦስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ምርቶችን ለውጭ ገበያ አቅርቧል፤**

*መንግሥት መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን* እውን ለማድረግ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ብሎ ትኩረት ከሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት አንዱ ነው:: የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሦስት ዋና ዋና መሠረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው:: እነዚህ ተልዕኮዎቻቸውም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራን ማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማከናወን ናቸው:: ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ሥራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል::

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብስበ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሠረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ:: ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም ሰፊ የሰውና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል::

በአሁኑ ወቅት በመላ አገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች እንደሚገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ:: ፓርኮቹ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ:: በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መናኸሪያ እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤቶች ተገኝተውበታል::

እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም በተጠናቀረ መረጃ መሠረት፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በቀጥታ በምርት ተግባራት ላይ 81ሺ ሠራተኞች ተሰማርተዋል:: ይህ አሀዝ ከፓርኮቹ ውጪ ያሉና ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን ሰዎች አይጨምርም:: በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ የሚገኙ አምራቾች ከፓርኮቹ ውጪ ካሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር የሥራ ትስስር ስላላቸው በዚህ ሂደትም በርካታ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል::

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሥራ ከጀመሩበት ጊዜ ወዲህ ከ61 ቢሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው ምርቶች ለአገር ውስጥና ለዓለም አቀፍ ገበያ ቀርበዋል:: በሌላ በኩል ፓርኮቹ ሥራ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ፣ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ፣ ለውጭ ገበያ የቀረበውና በተኪ ምርቶች የተገኘው ዋጋ አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ሆኗል:: ከዚህ ውስጥ፣ 930 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነው ገንዘብ ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች የተገኘ ገቢ ነው:: ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ተኪ ምርቶችን የማምረት ተግባርም (Import Substitution) ጥሩ ውጤት እየተመዘገበበት እንደሆነ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን መረጃዎች ያሳያሉ::

የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማፋጠን ብዙ አስተዋፅኦዎችን እያበረከቱ ቢሆንም፣ በሙሉ አቅማቸው እንዳያመርቱ መሰናክል የሚሆኑ የተለያዩ ችግሮች ሲያጋጥሟቸው ይስተዋላል:: በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተፈጠረው የፀጥታ መደፍረስ በጦርነቱ ቀጣና ውስጥ በሚገኙ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩ ይታወቃል:: የዚህ ችግር ሰለባ ከሆኑት ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ (Kombolcha Industrial Park) አንዱ ነው::

የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ በ90 ሚሊዮን ዶላር የተገነባና በ75 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሲሆን፣ ዘጠኝ ሼዶችም አሉት:: ከአንድ ሺ ሁለት መቶ በላይ ሠራተኞችም አሉት:: የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን አምርተው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አራት የደቡብ ኮሪያ፣ የኢጣሊያ፣ የአሜሪካና የቻይና አምራች ኩባንያዎች የገቡበት ይህ ኢንዱስትሪ ፓርክ፤ በ2014 ዓ.ም አሸባሪው ሕወሓት በአማራ ክልል በፈጸመው ወረራ ውድመትና ዘረፋ እንደተፈጸመበት ይታወቃል::

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎች ከዚህ ቀደም እንዳስታወቁት፣ በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ላይ የደረሰው ጉዳት በሁለት መልኮች የሚገለጽ ነው፤ የመጀመሪያው ዝርፊያ፤ ሁለተኛው ደግሞ ውድመት ነው። በዚህም የፓርኩ የቢሮ ዕቃዎችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) ሲስተሞች፣ የአምራች ኩባንያዎች ቢሮዎችና ቁሳቁስ፣ ለውጭ ገበያ የተዘጋጁ የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትና የቆዳ ውጤቶች ተዘርፈዋል። ወደ ፓርኩ ገብተው በምርት ሥራ ላይ ያሉ ድርጅቶች አምርተዋቸው የነበሩና ወደ ውጭ ሊላኩ የተዘጋጁ የተለያዩ ምርቶች ተሰርቀዋል። ኩባንያዎቹ የሚያመርቷቸውን ምርቶች ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችም ተወስደዋል።

በድርጅቶቹ ቢሮዎች ውስጥ የነበሩ መገልገያዎች፣ በቀላሉ ሊተኩ የማይችሉ መሣሪያዎችና የምርት ሥርዓቶች፣ አገልግሎት መስጫዎች፣ የደኅንነት መጠበቂያ መሣሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ እና ሌሎች ገመዶች፣ ለፓርኩ ተጨማሪ ግንባታ ለማድረግ እንደመጋዘን ሲያገለግሉ የነበሩ ኮንቴይነሮች፣ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ያሉ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ቁሳቁስ ተዘርፈዋል፤ወድመዋል:: አምራች ኩባንያዎቹ ለሥራዎቻቸው ያስገቧቸው መለዋወጫ ዕቃዎችና ሌሎች ጥሬ ዕቃዎች ከፍተኛ ውድመትና ዝርፊያ ተፈፅሞባቸዋል። የፓርኩ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎች፣ የማምረቻ ቦታዎች፣ የኬሚካል ማጣሪያ እና ሌሎች በፓርኩ ውስጥ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ክፍሎች ከፍተኛ ዝርፊያና ውድመት ደርሶባቸዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሳንዶካን ደበበ፣ የኮርፖሬሽኑን የ2014 በጀት ዓመት አፈፃፀም አስመልክቶ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ በሰጡበት ወቅት፣ «በሰሜን የአገሪቱ ክፍል የተከሰተው የሰላምና ፀጥታ መደፍረስ በኢንቨስትመንት ተግባራትና በኮርፖሬሽኑ ዓመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፤ የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ በጦርነቱ ከፍተኛ ውድመት ደርሶበት ነበር:: በኢንዱስትሪ ፓርኩ ላይ የደረሰው ጉዳት በሁለት መልኮች የሚገለፅ ነው:: አንደኛው የኮርፖሬሽኑ ሀብት የገጠመው ውድመትና ዝርፊያ ሲሆን፤ በፓርኩ ውስጥ በሥራ ላይ የነበሩ አምራች ድርጅቶች የደረሰባቸው ዝርፊያ/ውድመት ደግሞ የጉዳቱ ሌላኛው መልክ ነው» በማለት ገልጸው ነበር::

*መንግሥት* በባለሀብቶች ተመራጭ የሆነውን ይህን የኢንዱስትሪ ፓርክ ከደረሰበት ውድመት አገግሞ በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲመለስ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል:: በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኮሚዩኒኬሽንና ማርኬቲንግ መምሪያ ኃላፊ አቶ ሔኖክ አስራት፣ ኮርፖሬሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ያከናወናቸው ተግባራት የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከደረሰበት ውድመት አገግሞ በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲመለስ ስለማስቻላቸው ይገልፃሉ::

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ኢንዱስትሪ ፓርኩን በፍጥነት ወደ ሥራ ለመመለስ በኮርፖሬሽኑና ተባባሪ ባለድርሻ አካላት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ጉዳት የደረሰባቸውን መሠረተ ልማቶች የመጠገንና የሥነ ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ሠራተኞች የሥነ ልቦና አቅም ግንባታ ድጋፍ የማድረግ ሥራዎች ይጠቀሳሉ::

«የወደሙ መሠረተ ልማቶች ተጠግነው በድጋሜ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል:: ጦርነቱ ያስከተለው ሥነ ልቦናዊ ጫናም ቀላል ባለመሆኑ በፋብሪካዎቹ ውስጥ የሚሠሩት ሠራተኞች በጥሩ መንፈስ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ የሚያግዙ የሥነ ልቦና ግንባታ ሥራዎች ተሠርተዋል::» የሚሉት አቶ ሄኖክ፣ «ፋብሪካዎቹን ወደ ሥራቸው ለመመለስ የሚያግዙት የቅድመ ዝግጅት ተግባራት ሥራዎች ካለቁ በኋላም ወደ ምርት ሥራቸው ተመልሰዋል፤ ሁሉም አምራቾች ማምረት በሚችሉበት አቅም እያመረቱ ነው:: ምርቶቻቸውንም ወደ ውጭ እየላኩ ይገኛሉ» በማለት ይገልፃሉ::

እንደ አቶ ሄኖክ ማብራሪያ፤ የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ኩባንያዎችን ወደ ምርት ሥራቸው ለመመለስ ከተከናወኑ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት በተጨማሪ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ በምርት ሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙት ኩባንያዎች የተደረጉ ሌሎች ማበረታቻዎችም አሉ:: ከእነዚህም መካከል ለኩባንያዎቹ የተደረጉ የሼድ የኪራይ ጊዜ እፎይታና የኪራይ ምህረት ይጠቀሳሉ::

«በፓርኩ መሠረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ደርሷል፤ ተመርተው ወደ ውጭ ሊላኩ የተዘጋጁ ምርቶችና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ተዘርፈዋል» በማለት በፓርኩ ላይ የተፈፀመውን ውድመትና ዘረፋ ያስታወሱት አቶ ሔኖክ፣ ኢንዱስትሪ ፓርኩ በገንዘብ ሲሰላ ምን ያህል ውድመትና ዘረፋ እንደተፈፀመበት ጥናት የሚያደርጉ ከተለያዩ የመንግሥት አካላት የተውጣጡ ኮሚቴዎች ውድመቱንና ዘረፋውን እያጠኑ እንደሚገኙና የጥናት ሥራው ሲጠናቀቅ እንደሚገለፅ ጠቁመዋል::

የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሥራ እንዲመለስ ከሌሎች ኢንዱስትሪ ፓርኮች ድጋፍ እንደተደረገለት በፓርኩ የሥራ ኃላፊዎች ተገልጾ ነበር:: ፓርኩ እስከ መጋቢት 2014 ዓ.ም አጋማሽ ባሉት ወራት ወደ ውጭ ከላካቸው ምርቶች ከሰባት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት እንደቻለ የተገለፀ ሲሆን፤ ይህ አፈፃፀም ፓርኩ ከውድመትና ዘረፋው በኋላ ወደ ሥራ ተመልሶ ያከናወነውን ሥራም የሚጨምር ነው:: ከተገኘው ገቢ ውስጥ ሦስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላሩ ፓርኩ ካጋጠመው ውድመትና ዘረፋ በኋላ ወደ ሥራ ተመልሶ ካከናወነው የምርት ሥራ የተገኘ ነው:: ከሴት የእጅ ቦርሳ፣ ካልሲ፣ የወንድ ሙሉ ሱፍ፣ የስፖርትና ሌሎች አልባሳት ሽያጭ የተገኘው ይህ የፓርኩ ገቢ፣ ውድመቱና ዝርፊያው ተፅዕኖ እንዳሳደረበት ግልጽ ነው::

በቅርቡ የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክን የጎበኙት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ኢንዱስትሪ ፓርኩ በጦርነት ከደረሰበት ጉዳት በማገገም አሁን ያለበት ወቅታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚደነቅ መሆኑን ገልፀዋል:: በኢንዱስትሪ ፓርኩ እና በአምራች ኩባንያዎች ላይ የደረሰውን ጉዳት በአፋጣኝ በመጠገንና መልሶ በማቋቋም ወደ ምርት ሂደት ለማስገባት መስዋዕትነት የታከለበት ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ያስታወሱት የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሳንዶካን ደበበ፤ ፓርኩን ወደ ሥራ ለመመለስ የተከናወኑ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ውጤት በማምጣታቸው በአሁኑ ወቅት ኢንዱስትሪ ፓርኩ በጥሩ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል:: አምራች ኩባንያዎች የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለመቅረፍም ያልተቋረጠ ድጋፍ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግም ተናግረዋል::

ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል:: የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው:: የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው:: ስለሆነም የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመፍታትና አፈፃፀማቸውን በማሻሻል መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ማሳካት ይገባል::

# ስማኝ ምንም ቢያብድ ...

ምሕረት ሞገስ

‹‹በአሁኑ ጊዜ የትግራይ ሕዝብ ነገር ‹ጩኸት ለቁራ መብል ለአሞራ› እንደሚባለው ነው:: አንዱ ይደክማል፤ ይጮኻል፤ ይሞታል:: ሌላው ይበላል፤ ይጠቀማል:: የትግራይ ሕዝብ ጮኸ የኢትዮጵያ መንግሥትም ጩኸቱን ሰምቶ እርዳታ እንዲገባ ፈቅዶ እርዳታ ወደ ትግራይ ገባ:: ነገር ግን እርዳታውን የተቀበለው፣ የሚሰጠው እና የሚከለክለው፤ ለፈለገው የሚያከፋፍለው በእርዳታው የሚጠቀመው አሸባሪው ቡድን ነው::›› አለ ገብረየስ በምሬት::

የመሸታ ጓደኛው ዘውዴ ‹‹ፍሬ ነገሩን ትቶ የማይረቡና ጥቃቅኖቹን ማንሳት፤ የፈረስ ጭራ ስንጠቃ ጊዜን ከማጥፋት ውጪ ምንም ረብ የለውም:: ሕወሓት እንደሆነ ሲወለድ ያጠለቀውን የሚያወልቀው ሲሞት ነው:: ‹ድመት መልኩሳ አመሏን አትረሳ› እንደሚባለው ማለት ነው:: አሸባሪው ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ ዋነኛ ጠላት ነው:: ምንም ቢሆን ዓመል አያረጅም፤ ወያኔ ሲወለድ ጀምሮ ለትግራይ ሕዝብ የተሰጠ እርዳታን ሸጦ ጥይት የገዛ ጨካኝ መሆኑን የትኛውም የትግራይ ተወላጅ ደም ውስጥ የታተመ የማይረሳ ታሪክ ነው:: የማይማር ጠላት በእጅ ሲገኝ ደግሞ መቅጣት ነው:: ጠላት ሲገኝ በጥርስ እንጂ በልምምጥ አይሆንም::

ጠላት ምንጊዜም ጠላት ነው:: ምንም ቢያባብሉት ቂሙን ስለማይረሳ ወይም ስለማይተው ለጠላት መዘናጋት አይገባም:: የትግራይ ሕዝብም ቢሆን ጠላቱን ወያኔ ከጉያው አውጥቶ መጣል አለበት:: ይህንን ክፉ ጠላት በእጅ አስገብቶ በጥርስ መንከስ እንጂ መሬት አይንካህ እያሉ መለማመጥ እና ማሽሞንሞን አልፎ ተርፎ ቅዠቱ እንዲሳካለት መደገፍ በራስ ላይ እባብ መጠምጠም ነው:: ወደድከም ጠላህ ጠላቱን በጉያው ይዞ የሚያባብል እንደትግራይ ዓይነቱ ሰው አሁን እየፈፀመ ያለው እንዲያውም እባብ ሳይሆን ራሱ ላይ የሚጠመጥመው ዘንዶ ነው::›› አለና ገብረየስን ለመገሰፅ ሞከረ::

የዘውዴን ንግግር በእርጋታ ሲያዳምጥ የነበረው ተሰማ በበኩሉ ‹‹ትክክል ነው:: በአንድ ጊዜ ሁለቱንም የወደደ ሁለቱንም ያጣል:: ተረቱ እንኳን ሁለት የወደደ አንዱን ሳያገኝ ሔደ ነው፤ የሚባለው:: ብልጣብልጦቹ በከንፈራቸው እየሳቁ በጭካኔያቸው የትግራይን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብን ሲያስጨንቁ በዝምታ ማለፍ እና አንዳንዴም ከወያኔ ጎን ሆኖ መስዋዕትነት መክፈል ለመከራ ያለው መነኩሴ ዳዊቱን ሸጦ፤ አህያ ይገዛል የማለት ያህል ነው:: መነኩሴን የሚያስፈልገው ዳዊት ሆኖ ሳለ፤ ልክ ምርት ወደ ገበያ እንደሚወስድ ነጋዴ ወይም ጭነት እንደሚጭን ገበሬ ዳዊት ሸጦ አህያ መግዛትን እንደባህል ወይም አንዳንዴ እንደግዴታ መቁጠር ተገቢነት ያለው አይደለም::

የትግራይ ሕዝብ ሳይወድ በግዱ በወያኔ የፊጥኝ ተይዞ ለስቃይ ተዳርጓል። ‹‹ልጅ አምጣ፣ ስንቅ አቅርብ እየተባለ የቁም ስቃይ ያያል። መንግሥት ቢፈቅድም ሆነ ቢሰጥ አሁንም ቢሆን የትግራይ ሕዝብ ጋር እርዳታ ይደርሳል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው:: ራስ ወዳዱ፤ የሰውን ደም ለማፍሰስ የሚተጋው ቡድን የሚቀልበው ከእርሱ ጎን ቆመው የሚዋጉትን ነው:: ምናልባት እርዳታውን እንደአንድ ማታለያ ሊጠቀምበት ይችላል:: አሁን ስለእርዳታ መድረስ አለመድረስ ከመጨነቅ ይልቅ ዋናው ጉዳይ ይህንን አገርና ወገን ጠል የሆነ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት ማሳፈር እና ማጋለጥ፤ ከጎንህ አንቆምም በማለት መገፍተር ይገባል:: አሁን እኮ ሕዝቡም ግራ ገባው....›› አለና በረጅሙ ተነፈሰ ::

ገብረየስ በተሰማ እና በዘውዴ ተከታታይ ድብደባ የተፈፀመበት መሰለውና ትንሽ ቅር ተሰኘ:: ግን ደግሞ ሊሞግታቸው ፈልጓል:: የትግራይ ሕዝብ ወያኔን በጉያው የያዘበትን ምክንያት ለማስረዳት አዳገተው:: ሁለት ሃሳብ ብልጭ አለለት:: ሆኖም በምን መንገድ ያስረዳ? ‹‹ነገር ግን›› ብሎ ጀመረ:: ቀጠለና ‹‹ለማኝ ቢያብድ ስልቻውን አይጥልም፤ ምንም ዓይነት እክል ቢያጋጥም ዓላማን መሳት የማይሆን ነው:: በእርግጥ ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ለጦርነት፣ ለርሃብ እና ለሰቆቃ አስጥቶታል:: ይህንን ሳስብ ያመኛል:: እንዴት የወጣበትን ሕዝብ መጠቀሚያ ያደርጋል? እንዴት እስከ ሞት፤ ትውልድ እስከመፍጀት የሚያደርስ ዋጋ ያስከፍላል? ብዬ የጨከነበትን ምክንያት ለማስቀመጥ እቸገራለሁ::

ሕዝቡም አምኖ መቀበል ያቃተው ይህንን ነው::

> መሞት ካልቀረ ፈርቶ ሳይሆን ደፍሮ ቢሆን ተመራጭ ነው:: የዘላለም ጠላትን ደፍቶ መሞት ሞት አይደለም ሕይወት ነው:: እንዲህ እንደመዥገር ተጣብቆ ለዓመታት የትግራይን ደም ሲመጥ የኖረን ቡድን አጥፍቶ መሞት ትልቅ ጀግንነት ነው:: ጦርነት ውሎ ከፊት ለፊት ሆኖ ወገን አልገድልም ብሎ ወደ ኋላ ሲመለሱ በሕወሓት አጫፋሪ ከመገደል:: እዛው ከሕወሓት ጋር ተናንቆ ማለቅ ይሻላል::››

የትግራይ ሕዝብ ሕወሓትን ወልጃለሁ የሚለው እና የወለደው ነፃነቱን ለማግኘት እንጂ ራሱንም ሆነ ሌሎችን ለመጉዳት አይደለም:: ወይም ኢትዮጵያን ለማፍረስ አይደለም:: ነገር ግን ደግሞ እውነት እውነት ነው:: ሕወሓት የወጣው ከትግራይ ሕዝብ ነው:: ልክ ክፉ ልጅ እንደወለደች እናት የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት ክፋት እየተሰቃየ ነው:: ሕወሓት ትናንትም ዛሬም ትግራዋይን ከአጋም የተጠጋ ሲያለቅስ ይኖራል እንደሚባለው አድርጎናል::›› አለ::

ገብረየስ ቀጠለ፤ ‹‹ ሕወሓት ሲታሰብ ፖለቲከኞች እና ስልጣን ላይ ያሉ ሰዎችን በሙሉ ማሰብን ያስገድዳል:: የፖለቲካ ሰዎች ሲባሉ አንዳንዱ ስልጣን ብቻ ሲፈልግ፤ አንዳንዱ ሀብት ይፈልጋል:: አንዳንዱ ለሕዝብ እና ለአገር ሲያስብ፤ አንዳንዱ ለስልጣኑ እና ለክብሩ ሲል ይጨነቃል:: ፖለቲከኛ እና ባለስልጣን ብቻ ሳይሆን ታች ያለው ባለሞያውም ቢሆን አንዳንዱ ሲሠራ እና ሲታትር በሥራው ለመርካት ብቻ ሲሆን፤ ለአገሬ ምን ጠብ አደረግኩ ብሎ ሁሉንም ከአገሩ ጥቅም አንፃር ይመዝናል:: የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ይወጣል:: የአገር ፍቅሩን በአፉ ሳይሆን በተግባር በትጋት ሠርቶ ያሳያል:: አንዳንዱ ደግሞ በተቃራኒው ስለሚያገኘው ገንዘብ ብቻ በማሰብ የሥራ ጊዜውን ያባክናል::

አንዳንዱ ባለሙያ ሹመትን ሲፈልግ በስልጣን ዘመኑ ሊዘርፍ ስለሚችለው ገንዘብ እና ስለሚሰራው ቤት እያሰበ ይቃዣል:: ሀብት መፈለግ የፖለቲካኞች እና የባለስልጣኖች ብቻ ሳይሆን የብዙሃን ባለሞያዎችም ፍላጎት ነው:: የወያኔ ባለስልጣናት ደግሞ ጭንቀታቸው የሕዝብ እና የአገር ጉዳይ ሳይሆን፤ የራሳቸው ክብር፣ ስልጣናቸውን ማጣታቸው እና እንደፈለጉ የሚንደላቀቁበትን ገንዘብ ማግኘት አለመቻላቸው የሚያሳብዳቸው መሆኑ መለያ ባህሪያቸው ነው::

አሁንም ጭምር ለሕዝብ ሳይሆን ለራሳቸው ለስልጣናቸው፣ ለክብራቸው እና ቀጣይነት ያለው ዘረፋ ውስጥ መሰማራት ባለመቻላቸው ሕዝቡን ይማግዳሉ:: መዝረፍ ካልሆነላቸው አገር እስከማፍረስ የደረሰ ጥፋት ለመፈፀም ወደ ኋላ አይሉም:: አሁንም ጭምር እንደማይሆንላቸው እያወቁ ሕዝቡን ያወናብዳል:: ሕዝቡ ምን ያድርግ? ምን አቅም አለው? የትግራይ ሕዝብ ላይም ለመፍረድ ያስቸግራል::›› ሲል እያስተባበለ ጥያቄ አቀረበ::

ምላሽ አልጠበቀም በድጋሜ ሌላ ሃሳብ ጨመረ:: ‹‹ አሁን ላይ የትግራይ ሕዝብ ምንም እንኳን ቡድኑን ባይደግፍ ሊያደርግ የሚችለው ምን አለ? ምርጫ አጥቷል:: እነርሱ ዓላማቸው ስልጣን እና ዝርፊያ ብቻ ነው:: ለማኝ ምንም ቢያብድ ስልቻውን እንደማይጥለው ሁሉ እነርሱ ምንም እንኳ የእብደት ደረጃ ላይ ቢደርሱም ፅኑ ፍላጎታቸው በትግራይ ወጣት ደም ተጠቅመው ስልጣን የማግኘት ፍላጎታቸውን ሊተዉት አይችሉም:: ለዚህ ስልቻቸው ሲሉ እንኳን ሕዝቡ እራሳቸውም ቢሆኑ የትኛውንም ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ናቸው:: ›› አለ::

ገብረየስ ዛሬ ማንም እንዲያስቆመው የፈለገ አይመስልም:: ያለወትሮ አልፎ አልፎ ድምፁ ከቁመቱ በላይ እየተሰማ በምሬት መናገሩን ቀጥሏል:: ‹‹መፍረድ ቀላል ነው:: እያንዳንዳችሁ የትግራይ ተወላጅ ሆናችሁ ዛሬ ትግራይ የምትገኙ ቢሆን ኖሮ የምታደርጉት አሁን ካለው ሕዝብ ተመሳሳይ ነው:: ምክንያቱም ሕወሓትን ልቃወም ብትሉ ከሕወሓት የበቀል ጥርስ ማምለጥ ቀላል አይሆንም:: በኅብረት መነሳትም ቀላል አይደለም:: የሰው ልጅ አስተሳሰብ ፍላጎት እና የድፍረት ደረጃ የተለያየ ነው:: አንዱ ሲደፍር ሌላው ይፈራል:: የደፈረው ፈሪው ሳይደግፈው ወደ ኋላ ሲል የደፈረው ሕይወቱ እንደቀልድ ያልፋል:: የደፈረው ላይ እርምጃ ሲወሰድ ያየው ሌላኛው ለመድፈር ጫፍ ላይ ደርሶ የነበረው መልሶ ወደ ኋላ ይሸሻል:: የበለጠ መፍራት ይጀምራል::

ማንም ቢሆን ከመሞት በምንም መልኩ ቢሆን መኖርን ይፈልጋል:: በተረፈ የውጭዎቹም የትግራይ ተወላጆች አንዳንዶቹ የቀደመው የሕወሓት የጥቅም ተጋሪ በመሆናቸው፤ አሁንም ድረስ ሕወሓትን ደግፈው በአደባባይ ሳያፍሩ ሰልፍ ይወጣሉ:: አንዳንዶቹ ሕወሓትን ባይደግፉም አያገባንም ብለው ጥጋቸውን ይዘው ቆመዋል:: አንዳንዶች ደግሞ የሕወሓትን ሴራና ክፋት ሳያጣሩ እንዲሁም ድርጅቱ የትግራይ ተወላጅን ጭምሮ መላ ኢትዮጵያን ምን ያህል እንደጎዳ ሳያገናዝቡ በዘር ትግሬ ስለሆኑ ብቻ ‹ነገር ወዳጅ ከመንገድ ዳር ቅበሩኝ አለ› እንደሚባለው ተራ ወሬ ላይ አተኩረው መንግሥትን በመቃወም ጊዜ ያጠፋል::›› ሲል ዘውዴ ቆጣ ብሎ የገብረየስን ንግግር ለማስቆም ጥያቄ ማንሳት ጀመረ::

‹‹ደፍሮ ተባብሮ ሕወሓትን ነጥሎ አጋልጦ ስላልሰጠ ከሞት ያመለጠ ማን ነው? የትግራይ ሕዝብ ሕወሓት ይገድለኛል በሚል ስጋት ለመደገፍ ተገዷል ካልክ፤ ሕወሓትን ቢደግፍም በጦርነት እየሞተ ነው:: መሞት ካልቀረ ፈርቶ ሳይሆን ደፍሮ ቢሆን ተመራጭ ነው:: የዘላለም ጠላትን ደፍቶ መሞት ሞት አይደለም ሕይወት ነው:: እንዲህ እንደመዠገር ተጣብቆ ለዓመታት የትግራይን ደም ሲመጥ የኖረን ቡድን አጥፍቶ መሞት ትልቅ ጀግንነት ነው:: ጦርነት ውሎ ከፊት ለፊት ሆኖ ወገን አልገድልም ብሎ ወደ ኋላ ሲመለሱ በሕወሓት አጫፋሪ ከመገደል:: እዛው ከሕወሓት ጋር ተናንቆ ማለቅ ይሻላል::›› አለ ዘውዴ:: ይሔንን በሚመለከት ገብረየስ ምንም ማለት አልቻለም:: ለማሳመን መንገድ አጣ:: ቃላቶች አጠሩት::

የዘውዴን ምት መመለስ አቅቶት ሲያሰላስል፤ ተሰማ ተጨማሪ ሃሳብ መሰንዘር ቀጠለ:: ‹‹ በእውነት ይህንን በተለይ የትግራይ ጠላት የሆነን ድርጅት ሕዝቡ በትክክል ያወቀው አይመስለኝም:: በትክክል አውቆት ለማስወገድ የሚፈልጉ ካሉ ግን በጥቂቱ በጥቂቱ ይሞላል ልቃቂቱ ነው:: የፈለጉትን ሥራ ለማከናወን ስልት ነድፎ በጥንቅቄ አስቦ የሚንቀሳቀስ ካለ መፈፀሙ ሕወሓትም ላይነሳ መቀበሩ አይቀርም:: ለዚህ ደግሞ ጊዜ መስጠት አያስፈልግም:: ማንኛውም ተግባር መከናወን ያለበት በጊዜው እንጂ ጊዜው ካለፈ በኋላ መሯሯጥ ጥቅም የለውም::

በግ የሌለው ቀበሮ አውሬ አትመስለውም እንደሚባለው አንዳንዱ አሁንም ድረስ ሕወሓትን ያምነ ይኖራል:: ግን ደግሞ አስቀድሞ ማንንም የማይምር ዓላማውን ለማደናቀፍ የሚሞክረውን ብቻ ሳይሆን የከፋ ድርጊት ሲፈፅም የማይደግፈውንም ጭምር ለመጉዳት እና ለማጥፋት ወደ ኋላ የማይል መሆኑን ያልተገነዘበ ሰው ለወደፊት ችግር ያደርስብኛል ብሎ ባይጠረጥርም ተጎጂ መሆኑ አይቀርም:: ስለዚህ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለ የትኛውም ሰው ይህ አጥፊ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ቀንና ሌሊት የሚሠራ ቡድን በትግራይ ያለውን ተቀባይነት ሙሉ ለሙሉ እንዲያጣ ለማድረግ ጠንክሮ መሥራት ያስፈልጋል:: ምንም ቢሆን ተቀባይነት በሌለበት ቦታ አንድ ጉዳይ ለመፈፀም ያስቸግራል:: በዚህ በኩል የእነርሱን ያህል በትጋት አሁንም አልተሠራም:: ስለዚህ መሥራት አለባችሁ ›› አለው::

ገብረየስ ‹‹ትክክል ነው:: በቅርብ የሚኖሩ ሰዎች ላይተዋወቁ ይችላሉ:: በእርግጥም ዓይንና ጆሮ ቅርብ ለቅርብ ቢሆኑም ሳይተዋወቁ እንደሚኖሩት ሁሉ ሕወሓትእናየትግራይሕዝብሙሉለሙሉተዋውቀዋል የሚል እምነት የለኝም:: ሕወሓትን ላወቀው ‹አይነደረቅ ሌባ ከነቃጭሉ ይገባ› እንደሚባለው ኢትዮጵያን ሲዘርፍ የትግራይን ሕዝብ መነገጃ ሲያደርግ ኖሮ ያለምንም ይሉኝታ በድርቅና መልሶ ትግራይ ጉያ ስር መግባቱ ሲታይ፤ ትግራይዋዮች ቡድኑን አውቀውታል ለማለት ያዳግታል:: ደግሞ ሕወሓት በምንም መልኩ የትግራይን ሕዝብ ከመጥቀም ይልቅ ዕድሜውን በሙሉ የትግራይን ሕዝብ ዕርዳታ ሲሰርቅ፤ በሰረቀው የዕርዳታ ገንዘብ ጥይት ሲገዛ፤ የትግራይን ሕዝብ ደም ሲያፈስ እና ሲያስፈስስ ስልጣን ላይ ከወጣም በኋላ በስሙ ሲነግድ መኖሩን የሚያውቀው ሕዝብ ቁጥር ቀላል አይደለም::

አሁን ላይ የትግራይ ሕዝብ አሸባሪው ሕወሓት በሆነ መንገድ ከሕዝቡ ተነጥሎ ይለቅ ቢባል ዓይኑን ሳያሽ ደስ ብሎት የሚቀበለው ሃሳብ ነው:: ፍፃሜውንም በንቃት ይከታተላል ብዬ አምናለሁ:: እስከዚያው ግን የትግራይ ሕዝብ ላይ መፍረድ ያስቸግራል:: ሕወሓትን ለመቅበር የትግራይ ሕዝብ ሊተባበር ቢገባም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ኃላፊነቱን መወጣት አለበት::›› ሲል ተሰማ በበኩሉ የዕለቱ የመሸታ ቤት ውይይት ለዛሬ በዚህ ላይ እናብቃው ብሎ የጠጡበትን ለመክፈል እግሩን ዘርግቶ እየተንጠራራ ቀኝ እጁን ኪስ ውስጥ ከተተ::

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተለያዩ ከተሞች ‹‹ስለኢትዮጵያ›› የተሰኘ መድረክ ሲያካሂድ ቆይቷል፡፡ በመድረኮቹ በተለያዩ አገራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ በነዚህ መድረኮች ለውይይት በሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ትልልቅ ሰዎችም የውይይት መነሻ ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡ በመድረኩ ሲነሱ ከቆዩ በርካታ ጉዳዮች መካከል ኪነ ጥበባዊ ይዘት ባለው መልኩ በግጥም የተላለፉ ሃሳቦችም ይገኙበታል። እኛም በዛሬው የዘመን ጥበብ ዓምዳችን ቅርበት ያለውን እና በአንድ መድረክ ላይ የቀረበውን የአቶ መስቀሉ ባልቻን ግጥሞች እንደሚከተለው ሙሉውን አቅርበነዋል፡፡

## የተንቤኑ ተኩሳ

ከዋሻ መሽጎ ከምግባር መንኖ
እየዋለ ሲያድር ሰውኛ ጠፍቶበት
ሥነ-ምግባር ከድቶት
ሥም አውጪ ስም ሰጠው በግብር አስተካክሎ
"የተንቤኑ ተኩላ" በሰው አስመሥሎ
ጉድ አሰኘን እኮ ከሰው ተራ ውሎ
ለአዛውንት አይነገር በእምነት አይዘከር
ተለምኖ አያውቅ ክብር በርሱ አይኖር
ሰው ጤፉ ተባለ ኢጋንንት ሰፍኖበት
ሰው ነን ያሉ ሁሉ አብረው በአንድነት
ያገር ሽማግሌ ወጥቶ መከረበት
ሲያወጡ ሲያወርዱ በጣም ተቸግረው
ሄዱ ከመሠረት ማንነት ሊያጠኑ
ግድ ሆኖባቸው እናትን ጠየቁ
እናት በምላሿ ‹‹ልጅማ ልጄ ነው እኔም ቸግሮኝ ነው››
ዘመድ ወዳጆቼ ምን ይሆን ማርከሻው?
ጥያቄ ጠየቁ
አባት ጣልቃ ገቡ
‹‹ኧረ እንዲህ አይደለም የዚህ ልጅ ችግሩ
ከባዕድ ማበሩ ከባዕድ ማደሩ
ከኔ ነው ችግሩ›› ብለው መሰከሩ፡፡
ባይሆን ባይሆን ከዋሻ ሲገባ
የዋሻው ኢጋንንት መክሮት ይሆን ደባ?
ኧረ እንዲህ አልነበር የዚህ ልጅ ነገሩ
ከሰው ተራ ወጥቶ ከከፋት ማበሩ
ኑሮን ማማረሩ
ከኔው ነው ነገሩ ብለውት ጀመሩ።
የአንድ ጐረምሳ ዕድሜ ከዋሻው መኖሬ
ተፈጥሮን ከድቼ ከባህል ተጣልቼ
ከተንቤን ጥልቅ ዋሻ አይኖር ገብቼ
የተበዳይ አጋር ሐቅ አፋላጊ ሆኜ
ላነጋ ላወጋ እውነት ተከትዬ

መሰልኩ አስመስዬ ፍጥረት አማልዬ
አለሁ ከጐናችሁ ከቅንነት እሴት ጠባጠብ ተክዬ››
ብለው ሌላ አከሉበት
ሀብዬ ስጀምር አሥርቱን ትዕዛዛት
በአሉታ መንፈስ አሳየኝ ምልከት
‹‹ተው ተው ይህ ነገር
ምንም አትናገር
በዚህ በኛ ሰፈር
በዚህ በኛ ምድር
ሟችም አይታወቅ ገዳይም አይናገር
ካህን ጥምጣም የለ
መሠዋት ነው ታግሎ
አገር ማኅበረሰብ እራስን ነው መክዳት
ላልሰማው ማሰማት አይገቡ ውስጥ መግባት
የተንቤኑ ተኩላ ሕግ የለው አይገደድ
የያዘው ይዞ ከዱር መንጎዳጎድ
መሰዋት መማገድ
"ለምን" አይጠየቅ
ምንም አይታወቅ
ሂድ ሲሉህ መሄድ ነው
ሲያዝህም መታዘዝ
አሉ በመተከዝ
ተንቤን የጉድ ሠፈር
አለን ልዩ ምስጢር
አለማንገራገር አለመነጋገር
ፊትና ኋላህ ላይ እሳት ቢንጠረጠር
ጋንጃህን አሽትተህ ለመግባት መንደርደር
ይኸው የተንቤን ጉድ
የተንቤኑ ተኩላ አገር ላገር ሲሄድ
እራሱ ሲማግድ ነፃነትን ሲያነድ
ምነው ማለት የለ
እንዴት አይጠየቅ
ጋኔን ለክፎት ነው ከመሸገው ዋሻ
ሲወራ ሲያድር ከምሽጉ ጥሻ
የተንቤኑ ተኩላ በሰው ተመስሎ
ቢስሚላሂ የለ በስመአብ አይባል
የኛንም አይወስድ የለም የሱ ባህል
እናት ሴት መሆኗን
በአገር መመሰሏን
አያምን አያሳምን
ጠፍቶበት ሰው መሆን
የተንቤኑ ተኩላ ከሰው ተመስሎ
መስሎ አስመስሎ
በእንግድነት ገብቶ ለሆድ አስገድዶ
ቤተሰብ አግቶ ለስሜቱ ማግዶ
ልጅን ከአባቷ ፊት አስገድዶ ደፍሮ
ይህ አልበቃ ብሎት በደቦ ተዛዝሎ
አይሆነውን ሆኖ
ደግሞ ይባስ ብሎ
በያዘው ጠብመንጃ ገድሎ አስገድሎ
የተንቤኑ ተኩላ በሰው ተመስሎ
ጉድ አሰኘን እኮ ከሰው ተራ ውሎ
ነፃ አውጪ ነኝ አለ
ታጋይ ተጋደላይ ነኝ በማለትም ማለ
ቀርበን ስናያቸው
የሰው ቅርጽ እንጂ የሰው ግብር የላቸው፡፡
እልል ብለን ነበር ቀን እንደሚያወጡ
ከዋሻው ሲወጡ
ነገር ተገልብጦ ሲሰነባበቱ
ተኩላ ይሁን እፉኚት ጠፍቶን መለየቱ
ከዱር አራዊቱ ብሰው ተከሠቱ
ቢስሚላሂ የለ በስመአብን አያውቁ
ከጠብመንጃው በላይ ቂምን የታጠቁ፡፡

**በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት**
**በሐረር ስተካሄደው**
**የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይ**
**ከሽሽጉ አድማሱ አርሲ ሄ ጦሳ ወረዳ**
**2014 ዓ.ም**

## ትውልድን ነው ማከም

ሰው አልለው አውሬ
ተፈጥሮ ባገሬ
የራሱን ሞት ሞቶ መርዶ ያረዳኛል
ምሰሶና ካስማ ዋልታ ለሀገሩ
የዜጋ ጥላውን የሀገር ጠበቃውን
ሰሜን እዝን መታሁ እያለ ያቅራራል
የራሱን ሞት ሞቶ መርዶ ያረዳናል
መብረቅ ምት-መታሁት ብሎ ይፎክራል፡፡
ጉድ አሰኘንኮ ከሰው ተራ ውሎ
የተንቤኑ ተኩላ በሰው ተመስሎ
የአካሄድ መስመሩ ቋሚ መፈክሩ፤
ቤቱን ዱር አረጉ ወግ ማዕረጉን ሻሩ
ሚስት ከባሏ ፊት
ልጅን ከአባት እቅፍ ነጥቃችሁ ድፈሩ
እህል ስታገኙ ከቻላችሁ ብሉ
ተክል ካያችሁም እንዳያድግ መንጥሩ
የሚተርፍ ከሆነ በእሳት አቀጣጥሉ
የመኖሪያ ዕቃ ሰባብሩና ጣሉ
ምን ያረጋል ወንበር ሶፋ አልጋ ቅብጥሩ
ሰው መሆንን ጥሎ ከአውሬው መተባበር
የተንቤኑ ተኩላ የራሱ መፈክር
አጥፍቶ መጥፋት ነው ዜማ የሱ መዝሙር
ደግሞ ትምህርት ቤት
ምን ያረጋል ትምህርት
ጤና ጣቢያ ብሎ ሕክምና
አልጋ ማዋለጃ
ላቦራቶሪ ብሎ የሰው ማታለያ
ንቀሉና ጫኑ ኮምፒውተር አይተረፍ
እነሱ ይብቃቸው ከተንቤን ይታረፍ
የሰው ምስል የለው የተንቤኑ ተኩላ
ለመቀነስ እንጂ ደርሶ ለመጨመር ምንም የለው መላ
ድሮ የቀረ ስልት
ቤተ መቅደስ መስጂድ ምን ያረጋል እምነት
በኩነኔ በጽድቅ አስፈራርቶ መግዛት
ድሮ ቀርቷል
ሽማግሌ አሮጊት ለምን ይከበሩ
ለምንስ ይኑሩ
ክብር ውርደት ብለው ምግባር ከሚቆጥሩ
ለምንስ ይኑሩ
ይወገዱትና ሌሎች ይፈጠሩ
ያልኖሩ ይኑሩ
የተንቤኑ ተኩላ እንዲህ በልቶ በልቶ
እንዲህም አስልቶ
እፎይ ይላል በቃ አገርን አራቁቶ
ዕውቀትን ለመቅበር ትግሉ ተሳክቶ
በትግል አይጨምሩ ታግለው ያጎላሉ
የተንቤኑ ተኩላ እንዲህ ጉድ ያዘሉ
ከሰው ተራ ወጥተው ታጋይ ነን ይላሉ፡፡
ፍቅር ሰብዓዊነት ምን ያረጋል ስብከት
ጽድቅና ኩነኔ ያልሰከነ ኮተት
እንደ ዶሮ ፈንግል ፈንግለህ ተቀበል
ፈንግለህ ተበቀል፡፡
እቺ እኮ ናት ትግል
ምንም አታወላውል
እቺን ካልተገበርክ
ስምነው የተሸከምክ
እምኑ ላይ ታገልክ
ብሎ ሲወሰውስ
የተንቤኑ ተኩላ በሰው ተመስሎ
ጉድ አሰኘን እኮ ከሰው ተራ ውሎ
አያፍር አይነውር
በፀያፍ መፈክር ሀሳብ ሲሰነዝር
"ከእንስሳት ተጣላ ተኩስና ግደል
እሱ እየኖረ ነው እኛ የምንበደል
ነፃ አወጣ ምድሪቱን ዱር አድርገህ መንጥር እንኳን ሳይቀር
ጠላት ናቸው ብለህ እንስሳትን አባር
ጋንጃህን አሽትተህ ኃይልህን አጠናክር
ስበር ገነጣጥል የይሉኝታን አጥር
ከቻልክበት ሥፈር
አቅራራና ፎክር
የተንቤኑ ተኩላ የተንቤን እፉኚት
ጠባ ጠብ ቆስቁሰህ መግባባት አሽቀንጥር
ተንቤን የጉድ ሠፈር
ተንቤን የጉድ መንደር
አለው ልዩ ምክር አለው የሚዘከር
ውለታን እንዳትቆጥር
መግደል ምን አለበት
ማንም ሰው ይገላል
እስኪ ተመራመር
አዲስ ነገር ፍጠር
ከገደልክ በኋላ
አስከሬን ላይ ጨፍር
ቀሚስ ካየህ አትማር
መነኩሲቷን ድፈር
ሃይማኖትና እምነት ከምንም አትቁጠር
ስሜትህን ኰርኩር በስሜት ተሣፈር
ከጠባቧ ጐጆህ ከእኩያኑ ሠፈር
አታሞህን ደልቅ መዝሙርህን ዘምር
ዜማህን አንቆርቁር
ቁልቁለት ተንደርደር
ከባዕድ ነው መምከር!
ትልቅ ምን ያደርጋል ከትንሽ ተፋቀር
ከተንቤን ነው ማደር
ያው መጥፊያህን ቆምር
ኢትዮጵያ ሰማሽ የተንቤንን ዜማ
ልበ ትንሽ ልጅሽ ከባዕድ ሲስማማ
ዜጋሽን ሲያደማ
የአድዋ የዶጋሊ ታሪክሽ ላይሠማ
አልወርስም ሲል አየሽ?
ከታሪክሽ ሲሸሽ
ከዜሮ ሲጀምር የተንቤኑ ተኩላሽ
ባለ ዜሮ ድምር እፉኚቱ "ልጅሽ"?
የጀግኖችሽ አፅም ይጮሀሉ ከሩቅ
ከተንቤኑ ተኩላሽ ምንም አይጠበቅ፡፡
ካህኑም ማለለ ማለ አማማለ
በስምሽ ላይቀድስ ገዘትኳችሁ አለ፡፡
አንቺ ማህፀነ ለምለም
ታላቁ ሲታመም ታናሹን ነው ማከም
ወጣ ምንም ቢሆን ታሪክሽን አይረሳም፡፡
አይደልለው ጥቅም፡፡
ትውልድን ነው ማከም።

**በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት**
**ስደሴው ስተካሄደው**
**የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይ**
**ታኅሣሥ 10 ቀን 2014 ዓ.ም**
**ሽሽጉ አድማስ**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

# ልመናን እንደ ሀብት ማፍሪያ

**ሰላማዊት ውቤ**

ቀኑ መስከረም አምስት ዕለተ ሐሙስ ሲሆን ያገኘኋቸው መሀል መገናኛ ነው።እጅግ ሰብዓዊነት በጎደለውና በሚያሳዝን ሁኔታ የአሮጌ ማዳበሪያ ቅዳጅ በተነጠፈበት መሬት ላይ በግንባራቸው ተደፍተዋል። ድምፃቸው ይሰማ እንጂ የፊታቸው ገጽታ አይታይም። እግሮቻቸው፣ እጆቻቸውና ወገባቸው ከተፈጥሮ አቀማመጥ ውጪ በመሆናቸው የበርካታ አካል ጉዳተኝነት ተጠቂ ናቸው።

"ስለ አቦዬ በሽተኛ ፤ያላችሁን ጣል ጣል አድሩልኝ" ሲሉ የሚያወጡት የልመና ድምጽ በለሆሳስ ይሰማል።ለእግዜር ያለም ኪሱን እየፈተሸ ያለውን እየጣለ ይሄዳል።እኔም ቦርሳዬን ፈትሼ ጥቂት ብሮችን ጣል ካደረግኩ በኋላ ጎንበስ ብዩ፡-

‹‹ እባኮትን አባቴ ላናግሮት ፈልጌ ነበር››

በጥርጣሬ እና በመደናገር ስሜት ከተመለከቱኝ በኋላ በደከመ ድምጽ

‹‹ ምን ፈልገሽ ነው ?›› በማለት ሽቅብ እየተመለከቱ ጠየቁኝ

‹‹በአሁኑ ወቅት ልመና በአዲስ አበባ እየተስፋፋ መጥቷል። ለዚህ ደግሞ አንዳንድ ግለሰቦች ሰዎችን እያታለሉ ወደ ልመና እንዲገቡ እያደረጉ ነው የሚል መረጃ ስላለ የሚያውቁትን እንዲነግሩኝ ነው›› የሚል ጥያቄ አቀረብኩ።እርሳቸውም ፊታቸው በድንገት ተቀያይሮ‹‹ ታዲያ እኔ ምን አውቃለሁ፤የሚመለከተውን ሰው ሄደሽ ጠይቂ እንጂ ››ብለው አንባረቁብኝ። እርሳቸውን እንዳናግር የጠቆመኝን በመገናኛ አካባቢ ሱቅ በደረቴ ከሚሰራ ወጣት ጋር በመሆን ማግባባት ያዝን። ከብዙ ሙግትና ማግባባት በኋላ የሚያውቁትን አጫወቱኝ።

ስማቸው ሰማ ሴብሮ እንደሚባል ነገሩን።የአካል ጉዳቱ ሲወለዱ የነበረ ነው።የአካል ጉዳተኝነታቸውን የተመለከተ ሰው አዲስ አበባ ብትሄድ ትጠቀማለህ ስላላቸው ከማያውቁት ሰው ወደ አዲስ አበባ መጡ። ለከተማዋ አዲስ በመሆናቸው የት እንደሚያርፉ እንኳን አያውቁም። ሆኖም ይዟቸው የመጣው ሰው ለአንድ ሰው አስረከባቸው።የተረከባቸው ሰውም መጠለያ ሰጣቸው።ከጥቂት ቀናት በኋላም በአዲስ አበባ የተለያዩ ቦታዎች ላይ እየወሰዳቸው ያስለምናቸው ጀመረ።

በሌሊት እያስነሳቸው ወደ ተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች በመውሰድ ሲያስለምናቸው ይውልና ሲመሽ እንደገና መጥቶ የለመኑትን ገንዘብ ቆጥሮ ይረከባቸዋል። አንዳንድ ጊዜም ገንዘቡ ጠርቀም ሲል በሰዎች ምሽትን ሳይጠብቅ ሰብስቦ ይወስዳል።

ሆኖም አቶ ሰማ ሴብሮ ይህ ሕይወት አላስከፋቸውም። ቢያንስ በተወለዱበት አካባቢ የእለት ጉርሳቸውን ለመሸፍን ይቸገሩ ነበር።እጅና እግራቸውም ስለማይታዘዙላቸው የሚያበላቸውና የሚያንቀሳቅሳቸው ሰው ማግኘት ችግር ነው።አሁን ግን የተረከባቸው ሰው ቢያንስ ጧትና ማታ ከማደሪያቸው እያንቀሳቀሰ በመኪና የሚለምኑበት ቦታ ያደርሳቸዋል። እራታቸውንም አንድ ዳቦ ይሰጣቸዋል። አንዳንዴ የሚያስለምናቸው ሰውዬ ሳይመጣ ይውላል። ሆኖም ምንም ቢመጣ አመሻሽ ላይ ሳይመጣ አይውልም።



ሆኖም በመገናኛ አካባቢ በአቶ ሰማ ሴብሮ ላይ የሚፈጸመውን ህገ ወጥ ድርጊት የተመለከቱ ወጣቶች ግለሰቡን በፖሊስ ለማስዝ በመሞከራቸው ሰውዬው ፈርቶ ከአካባቢው ተሰወረ።እርሳቸውም የአካባቢው ወጣቶች በመከሩዋቸው መሰረት ግለሰቡ ሊጠጋቸው ሲፈልግ ለፖሊስ እናገራለሁ ብለው በማስፈራራታቸው አሁን ነጻ ወጥተዋል።ከሰውዬው መራቅ ስለፈለጉም ማርያም ወንዝ አካባቢ ከመሰሎቻቸው ጋር የላስቲክ ቤት ተከራይተው ህይወታቸውን መግፋት ቀጥለዋል።አሁን በልመና የሚያገኙትን ገንዘብ የሚቀማቸው ሰው ባለመኖሩ ደስተኛ እንደሆኑ ይናገራሉ።

በመዲናችን አዲስ አበባ ዋና ዋና ቦታዎች እንዲህ ዓይነቱን ትእይንት ማየት እየተለመደ መምጣቱን አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ ይደመጣሉ። አካል ጉዳተኞችንና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቅመው ልመናን የገቢ ምንጭ ያደረጉ አንዳንድ ራስ ወዳድ ግለሰቦች በጠራራ ፀሐይ እየፈፀሙት ያለ ሕገወጥ ተግባር ነው። በዚሁ ዙሪያ ያነጋገርናቸውና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያና መከታተያ ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ከማል ችግሩ መኖሩን ያረጋግጣሉ።

በመዲናዋ በአንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች ልመና እንደ ንግድ ሥራ የተቆጠረበት ሁኔታ ይስተዋላል።ሰው ቤት ተቀጥረው ወይም ሌላ የጉልበት ሥራ መሥራት የሚችሉት ወደ ልመና ይወጣሉ እንጂ አይሰሩም።መንገድ ላይ ህፃናት እየተለመነባቸው ነው። የአካል ጉዳተኞችም ሲለመንባቸው ይታያል።በተለይም የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸውን ግለሰቦች አድኖ በመፈለግ እና ከተለያዩ ክልሎች በማስመጣት ለልመና ማሰማራትና ገቢ ማግኘት የተለመደ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል።

የኔ ቢጤዎችን ለልመና የሚያሰማሩ ግለሰቦች መኪና ያላቸው ሀብታሞች ናቸው።አካል ጉዳተኞቹ አደባባይ መጥተው መቀመጥ የሚችሉ ባይሆኑም አምጥተው አስቀምጠዋቸው ይሄዳሉ። ማታም መጥተው ሲሰበስቡ የዋሉትን ገንዘብ ይወስዱባቸዋል።ለእነሱ ሽርፍራፊ ዳቦና የመጠለያ አገልግሎት እየሰጧቸው በቀን በርካታ ገንዘብ ሲሰበስቡ የሚውሉ ግለሰቦች እንዳሉ አቶ መሃመድ አልሸሸጉም።

ብዙዎቹ በልመና ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ግለሰቦች የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ሳይሆኑ በራሳቸው በሰዎች አማካኝነት ከክልል የመጡ ናቸው። በተደረገ ጥናት መሰረት ከነዚህ በልመና ከሚተዳደሩት የሕብረተሰብ ክፍሎች ችግረኞች ያልሆኑ እንዳሉ በጥናት ተለይቷል።በመሆኑም ወደፊት ችግሩን በሕግ ማዕቀፍ የመፍታት ሀሳብ መኖሩንም ያወሳሉ።

አቶ መሐመድ እንደሚያብራሩት፤ ቢሮው የአካል ጉዳተኞችና የተለያዩ የከተማዋ ነዋሪዎች የዕለት ጉርስ በማጣትና በተለያየ ችግር ምክንያት ወደ ልመና እንዳይወጡ ይሰራል።የገቡትም ከልመና እንዲወጡና ተሳትፏቸውንም በተለያየ መንገድ እያጠናከረም ይገኛል። የሴፍቲኔት መርሐ ግብር አንዱ ነው። በመርሐ ግብሩ መሥራት የማይችሉት በቀጥታ ድጋፍ ይረዱበታል።በሂሳብ ቁጥራቸው ብር ይገባላቸዋል።በአንድ ሰው 300 ብር ያገኛሉ።መሥራት የሚችሉት ደግሞ የሚጠቀሙበት መርሐ ግብር አላቸው።በሳምንት የተወሰነ ቀን ይሰራሉ። በሰሩት ሥራ ልክ ብር ያገኛሉ።

ሆኖም በሰዎች አማካኝነት ከተለያዩ ክልሎች እየመጡ በልመና ተግባር ውስጥ የሚሰማሩ ሰዎች እየተበራከቱ መምጣታቸው ስራቸውን አስቸጋሪ እንዳደረገባቸው ይናገራሉ።በዚህም ላይ በመዲናችን የኩላሊት በሽተኛ ያልሆነ የኩላሊት በሽተኛ ነው እየተባለ በመኪና በማዞር የሚለመንበትም እንዳለ ሁሉ የኩላሊት በሽተኞችን በመፈለግ ጭምር ትርፍ የጋራ የሚሰሩ ሰዎች እንዳሉም አረጋግጠዋል።

በአጠቃላይ በልመና የተለየ ጥቅም ለማግኘት የሚጥሩ ሰዎችን በመከታተል ለህግ ለማቅረብ ከጸጥታ አካላት ጋር ስራዎች ተጀምረዋል።ሰዎች ከልመና ይልቅ በላባቸው ሰርተው እንዲኖሩ ግንዛቤ መፍጠር ስራም እየተከናወነ ነው።ሆኖም ችግሩ ውስብስብ በመሆኑና የህግ ድጋፍም የሚያስፈልገው በመሆኑ አስተማሪ ቅጣት ማሳረፍ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ስራዎች ተጀምረዋል።

ከዚህ ባሻገር ግን ችግረኛ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትም የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት የተሰኘ ፕሮጀክት በቀጣዩ ጥቅምት ወር ይቋቋማል። በጀትም ተመድቦለታል።ጥምረቱ ችግሩን ይቀርፋል ተብሎ ይታሰባል ሲሉ አቶ መሐመድ ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።

# ዓለም አቀፍ




## አራት ግዛቶች ሩሲያን ለመቀላቀል ውሳኔ አሳለፉ

ዶኔስክ፣ ሉሃንስክ፣ ኬርሶን እና በደቡባዊ ዩክሬን የምትገኘው ዛፖሮዢያ ወደ ሩሲያ መጠቃለል እንደሚፈልጉ ባካሄዱት ሕዝበ ውሳኔ አረጋግጠዋል፡፡ በሉሃንስክ የተካሄደው ሕዝበ ውሳኔ ድምጽ ቆጠራ የተጠናቀቀ ሲሆን ከ98 በመቶ በላይ የሚሆኑት ነዋሪዎች ወደ ሩሲያ መጠቃለል እንደሚፈልጉ መወሰናቸው ተገልጿል።

በተመሳሳይ ከ99 በመቶ በላይ የሚሆኑት ዶኔስካውያንም ወደ ሩሲያ መጠቃለል እንደሚፈልጉ ከድምፅ ቆጠራው ውጤት ማወቅ ተችሏል ነው የተባለው፡፡ ዛፖሮዢያ እና ኬርሶንም በተከታታይ 93 እና 87 በመቶ በሆነ ድምፅ ከዩክሬን ተነጥለው ከሩሲያ ጋር መዋሃድ እንደሚፈልጉ አስታውቀዋል፡፡

አሁን የመጡትን አዲስ ክልሎች ወደ ሩሲያ ለማካለል የፓርላማውን እና የፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲንን ይሁንታ ማግኘት እንዳለበት አር ቲ ዘግቧል፡፡ የክሬምሊን ቃል አቀባይ ዲሚትሪ ፔስኮቭ ውሳኔው የብዙኃኑ ስለሆነ ሁሉም ነገር በፍጥነት እንደሚፈጸም ያላቸውን ተስፋ መግለጻቸውን ኤፍቢሲ ጠቅሶ ዘግቧል።

ሩሲያ በዩክሬን የጀመረችው ጦርነት ስድስተኛ ወሩን አስቆጥሯል። ብርቱ ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ቀውስ ያስከተለው ጦርነት ሰሞኑን ወደ ነዳጅ ግብይት የመሻገር አዝማሚያ እያሳየ ነው። ሩሲያ ለፖላንድ እና ቡልጋሪያ የምታቀርበውን ነዳጅ በሩብል ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል ምክንያት አቋርጣለች።

ዩክሬን የኔቶና የአውሮፓ ህብረት ተቋማት አባል ለመሆን የምታደርገውን እንቅስቃሴ ክፉኛ ስትቃወም የቆየችው ሩሲያ የኔቶ መስፋፋት ለህልውናዋ ከባድ ስጋት መደቀኑን በመግለጽ ዩክሬይን ከድርጊቷ እንድትታቀብ ደጋግማ ስታስጠነቅቅ ቆይታለች።

ከዚህ ሌላ የራሳቸውን ግዛት ለመመስረት የሚታገሉት የሩሲያ ቋንቋ ተናጋሪዎቹ የዶኔስክ እና የሉሃንስክ ሕዝቦች በዩክሬን የጸጥታ ኃይላት የሚደርስባቸው ጥቃትና የሙብት ጥሰት እንዲገታና የነጻነት መብታቸው እንዲከበር ፍላጎት እንዳላትም በተለያዩ ጊዜያት ገልጻለች። ይህን ታሳቢ በማድረግ ነው ሩሲያ በተቆጣጠረቻቸው አካባቢዎች ህዝበ ውሳኔ እንዲካሄድ ያደረገችው፡፡

## ኢራን ውስጥ በሚካሄደው ተቃውሞ የሟቾች ቁጥር 76 ደረሰ



በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋለች ሴት ሕይወት ማለፍን ተከትሎ ኢራን ውስጥ በተፈጠረ ረብሻ ቢያንስ 76 ተቃዋሚዎች በፀጥታ ኃይሎች መገደላቸውን አክቲቪስቶች ገለጹ። መቀመጫውን ኖርዌይ ያደረገው የኢራን ሰብአዊ መብቶች ድርጅት (አይኤችአር) ተቃዋሚዎችን ለማፈን ያልተመጣጠነ ኃይል እና ጥይቶችን ተጠቅመዋል ሲል ባለሥልጣናትን ከሷል።

የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በርካታ የፀጥታ ኃይል አባላትን ጨምሮ የሟቾች ቁጥር 41 መድረሱን ገልጸዋል። ለችግሩም "ሁከት ፈጣሪዎች" ያሏቸውን ወቅሰዋል። በተጨማሪም 20 ጋዜጠኞችን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም ታስረዋል። የአይኤችአር ዳይሬክተር ማህሙድ አሚሪ-ሞጋዳም "በተቃዋሚዎች ላይ የሚደርሰው ስቃይ እና እንግልት ከባድ ነው። በተቃዋሚዎች ላይ ጥይት መጠቀም ዓለም አቀፍ ወንጀል ነው። ዓለም የኢራንን ሕዝብ መሠረታዊ የመብት ጥያቄዎች መጠበቅ አለበት" ብለዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት የሰብዓዊ መብት ጽህፈት ቤትም የኃይል እርምጃው በእጅጉ እንዳሳሰበው ገልጾ፤ ባለሥልጣናት በሠላማዊ መንገድ የመቃወም መብትን እንዲያከብሩ አሳስቧል። የማህሳ አሚኒ የቀብር ሥነ ሥርዓትን ተከትሎ የፀረ-መንግሥት ሰልፎቹ ከ80 በላይ በሚሆኑ የኢራን ከተሞች ተስፋፍቷል።

የ22 ዓመቷ ወጣት ዋና ከተማዋን ቴህራንን እየጎበኘች በነበረበት ወቅት ነው ሴቶች ፀጉራቸውን በሒጃብ እንዲሸፍኑ የሚደነግገውን ጥብቅ ሕግ በመተላለፍ በሥነ ምግባር ተቆጣጣሪ ፖሊሶች የተያዘችው። "ለትምህርት" ወደ ማቆያ ጣቢያ ከተወሰደች በኋላ ተፈጸመባት በተባለ ድብደባ ለሦስት ቀናት ኮማ ውስጥ ቆይታ ሆስፒታል ውስጥ ሕይወቷ አልፏል።

አሚኒ በድንገተኛ የልብ ድካም ሕይወቷ ማለፉን ፖሊስ ቢገልጽም ቤተሰቦቿ የፀጥታ ኃይሎች ድብደባ እንደፈጸሙባት በመግለጽ የፖሊስን ሪፖርት ውድቅ አድርገዋል። በወጣቷ ሞት ምክንያት በፍጥነት የተቀሰቀሰው የሞራል ፖሊስ እና የሒጃብ ሕግ ተቃውሞ በኢራን ለዓመታት ካጋጠመው ከባዱ ፈተና ሆኗል።

ሰኞ ዕለት ቴህራን ጨምሮ በሌሎች በርካታ ከተሞች የተቃውሞ ሰልፎች መደረጋቸው ታውቋል። ከ20 በሚበልጡ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ተማሪዎች እና መምህራን የሥራ ማቆም አድማ አድርገዋል። የኢራን የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ የኢንተርኔት መቋረጥ የደረሱ ጉዳቶችን በተመለከተ ዘገባውን እንዳዘገየበት ጠቅሶ፤ በ14 ግዛቶች የ76 ሰዎች ሕይወት ማለፉን ገልጿል። ከእነዚህም መካከል ስድስት ሴቶች እና አራት ህጻናት ይገኙበታል።

ከሟቾች መካከል 35ቱ ከቴህራን በስተሰሜን በሚገኙት በማዛንድራን እና በጊላን ግዛቶች ነው። 24ቱ ኩርዶች በሚበዙባቸው ምዕራብ አዘርባጃን፣ ከርማንሻህ፣ ኩርዲስታን እና ኢላም ግዛቶች መሆናቸውንም የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት



## ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ነገ ይጀመራል

ቦጋለ አበበ

የ2015 ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የመጀመሪያ ዙር ጨዋታዎች በተሻሻለው አዲስ የውድድር መርሃግብር መሰረት ነገ በባህርዳር ስቴድየም በሚደረጉ ሁለት ጨዋታዎች ይጀመራል። የጣና ካፕ ውድድር ዋንጫ ከቀናት በፊት ባህርዳር ስቴድየም ላይ ማንሳት የቻለው ወልቂጤ ከተማ በአርባምንጭ ከተማ ቀን ሰባት ሰአት የሚያደርጉት ጨዋታ የውድድሩ መክፈቻ ሲሆን አስር ሰአት ላይ ባህርዳር ከተማ ኢትዮ ኤሌክትሪክን እንደሚገጥም አዲስ ከወጣው መርሀ ግብር ለማወቅ ተችሏል።

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማኅበር የ2015 ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ መርሐ-ግብር ዕጣ የማውጣት ፕሮግራምን ባሳለፈው ሐምሌ 26 ቀን በፅ/ቤቱ አዳራሽ ቀንና የውድድር ቦታውን ሳይገልፅ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። በወቅቱ በወጣው ፕሮግራም መሠረት በ5ኛ ሳምንት ቅዱስ ጊዮርጊስ ከኢትዮጵያ ቡና፣ በ6ኛ ሳምንት ፋሲል ከነማ ከቅዱስ ጊዮርጊስ እንዲሁም በ14ኛ ሳምንት ፋሲል ከነማ ከባህር ዳር ከተማ ጋር እንደሚገናኙ ተገልፆ ነበር።

ይሁን እንጂ አዲስ ይፋ በተደረገው የውድድር መርሀ ግብር የ2015 የውድድር ዘመን የ1ኛው ዙር መርሐ-ግብር ከላይ በተጠቀሱት ጨዋታዎች ላይ ማሻሻያ መደረጉ ታውቋል። ይህ መሆኑ ደግሞ በስፖርት ቤተሰቡ ዙሪያ የመቀየሩ ምክንያት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄን አስነስቷል። ለዚህም ጥያቄ ለሶከር ኢትዮጵያ ምላሽ የሰጡት የሊጉን አክስዮን ማኅበር ሥራ-አስኪያጅ አቶ ክፍሌ ሰይፈ፣ " የሁለት ዓመት የውድድር ዘመናችን ምን እንደሚመስል ከሱፐር ስፖርት ጋር ግምገማ አድርገናል። ብዙ ጠንካራ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ ሦስት ነገሮች ላይ አተኩረን መስራት እንዳለብን ተስማምተን አቅጣጫም ተሰጥቶበት ተለያይተናል። አንደኛው በጨዋታዎች ላይ ስታዲየም የሚገኙ ተመልካቾች ውስንነትን አይተናል። እግር ኳስ ያለ ተመልካች ምንም አይነት መስብ እንደሌለው በማሰብ በርከት ያሉ ደጋፊዎች ያሏቸውን ክለቦች ውድድሩ ለሚዘጋጅበት ከተማ ቅርብ ማድረግ እንዳለብን ተስማምተናል። በዚህም መሠረት የሀገሪቱ ትልቁ ደርቢ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከኢትዮጵያ ቡና ጨዋታ አስቀድሞ በወጣው መርሐ-ግብር መሠረት በ5ኛ ሳምንት ባህር ዳር ላይ ቢሆንም የሚኖረው ተመልካች ውስን ነው። አዳማ ብታደርገው ግን ጨዋታው በብዙ ሺ ተመልካች ታጅቦ የሚካሄድ በመሆኑ ለመቀየር ተገደናል" ብለዋል።

በተመሳሳይ ፋሲል ከነማ ከቅዱስ በ6ኛ ሳምንት ድሬዳዋ ቢደረግ የሚኖረው ተመልካች ጥቂት መሆኑ ነው። ባህር ዳር ቢሆን የሚኖረው ተመልካች በርካታ መሆኑን ከግምት በማስገባት መርሃግብሩ ተስተካክሏል። አሁን ፋሲል ከጊዮርጊስ ነው ባህር ዳር የሆነው በቀጣይ ደግሞ ሁለተኛው ዙር ሲመለስ የጊዮርጊስን ጥቅም በጠበቀ መልኩ አዲስ አበባ ከሆነ ሊያገኘው ይችላል። ካልሆነ ግን ቅርብ በሆነው በርከት ያሉ ደጋፊዎቹን በሚያገኙበት ከተማ አዳማ ሊያገኘው ይችላል። በዚህ ውድድሮች ተመልካች ሊኖራቸው ይገባል። ተመልካች ሊኖራቸው እንዲገባ ደግሞ ተመልካች ያለበት ቦታ ውድድር ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ መነሻነት መርሐ-ግብሩ ላይ ማስተካከያዎች ሊደረጉ እንደቻሉ ስራአስኪያጁ አብራርተዋል። ወደ ፊትም ገበያውን መሠረት ባደረገ መልኩ ተመሳሳይ ለውጦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ጠቁመዋል።




እንደ ስራአስኪያጁ ገለጻ፤ ይህ አይነት አሰራር ለሊግ ካምፓኒው ሳይሆን ጥቅሙ ለክለቦች ነው። ለምሳሌ ባህር ዳር ከተማ ከፋሲል ከነማ አስቀድሞ በወጣው ፕሮግራም መሠረት ከሆነ በ14ኛ ሳምንት አዳማ መጫወት ነበረባቸው፤ ግን ይሄ ብዙ ተመልካች ሊኖረው የሚችል ጨዋታ በመሆኑ ወደ 3ኛ ሳምንት በማምጣት ባህር ዳር ላይ እንዲካሄድ ተደርጓል።

ሁለተኛ ማሻሻያ የተደረገበት ጨዋታ መጀመሪያ ሰዓቱ ለተመልካች አመቺ አለመሆኑን በመረዳት የተቀየረ ነው። አቶ ክፍሌ እንደገለጹትም፤ ለምሳሌ የአራት ሰዓት ጨዋታ ከዚህ በኋላ የሚቀር ይሆናል። ይህ ሰዓት ሊጉ እንደ መጀመሪያ መሆኑ መጠን ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል። ከዚህ በኋላ ግን ተመልካች የሚስብ ብዙ ተመልካች ያለው ውድድር መሆን እንዳለበት በማመን ሜዳቸው መብራት የሌላቸው ከተሞች ጨዋታዎቹ ሰባት እና አስር ሰዓት እንዲሆኑ እና መብራት ያላቸው ሜዳዎች ደግሞ ዘጠኝ እና አስራ ሁለት ሰዓት እንዲሆኑ ተደርጓል።

ሦስተኛው ማሻሻያ የተደረገው ውድድሩን የሚያዘጋጁ ከተሞች ከዚህ ቀደም የመክፈቻ ጨዋታዎችን አያደርጉም ነበር። አሁን በተደረገው ለውጥ ሦስቱም ከተሞች ባህር ዳር፣ ድሬዳዋ እና አዳማ የመክፈቻ ጨዋታቸውን እንዲያደርጉ ነው። ይህም ከሱፐር ስፖርት ጋር በተደረገው ውይይት መሰረት የመጣ መልካም ለውጥ መሆኑን ተናግረዋል።

በአጠቃላይ ውድድሩን የሚመራው አክሲዮን ማህበሩ ዘንድሮ በጠንካራ ሁኔታ ወደ ገብያ የሚገባበት ጊዜ እንደሚሆን አቶ ክፍሌ የጠቆሙ ሲሆን፤ በዚህም ከፍተኛ የሆነ የቅስቀሳ ስራዎችን በተለያዩ መንገዶች እንደሚሰሩ ገልጸዋል። የሊጉን ጥራት እና ዕድገት ለመጠበቅም ሰፊ ስራ ይሰራል ብለዋል። በዚህ ስራ ውስጥ አንዱን ክለብ ለመጥቀም ሌላውን ለመጉዳት የሚሰራ ስራ አለመኖሩን ሁሉም ሊገነዘበው እንደሚገባም አክለዋል።


### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ዶ/ር አብዱል ስመድ ሐጂ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ዳንኤል ታደሰ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 167623 በ9/6/2013 ዓ.ም፤ 11/02/2014 ዓ.ም እና በመ/ቁ 161818 በ24/10/2013 ዓ.ም፤19/6/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤ.ቁ. ሮሆቦት የመኪና ማቆሚያ የሠ/ቁ 1-10931 አ.አ የሆነ መኪና የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 80,000 (ሰማኒያ ሺ. ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ኅዳር 5 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3:30 ሰዓት ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች**
**የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

### የንግድ ምልክት ምዝገባ እድሳት ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም፡- ዩኒሌቨር ፒኤልሲ (Unilever PLC)<br>የአመልካች አድራሻ:- Port Sunlight, Wirral, Merseyside, United Kingdom | | |
| 2 | የዕድሳት ዘመን፡- ከ 02/11/2013 ዓ.ም. እስከ 02/11/2020 ዓ.ም. | | |
| 3 | ምልክት፡- **GEISHA** | 4 | የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/4004 |
| | | 5 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 3 |
| 6 | የንግድ ምልክቱ የቀለም ዓይነት፣ የብቸኝነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ካለ እና የሚሸፍናቸውን ምርቶች ለማወቅ ሚያዝያ 14 ቀን 2007 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቮልዩም LXXIV ቁ. 224 የወጣውን የምዝገባ ማስታወቂያ ይመልከቱ፡፡ | | |
| | ምዝገባው ጸንቶ በሚቆይበት ወቅት፣ ባለቤቱን ሳያስፈቅድ፣ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሰራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ላይ በሕግ ክስ እንደሚመሠረትበት እናሳውቃለን፡፡ | | |

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-019 19/1/2015 (29/9/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ እድሳት ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም፡- ማኬይን ፉድስ ሊሚትድ (McCain Foods Limited)<br>የአመልካች አድራሻ:- 8800 Main Street, Florenceville-Bristol, New Brunswick E7L 1B2, Canada | | |
| 2 | ምልክት፡- McCain | 3 | የዕድሳት ዘመን፡-ከ14/11/2013 ዓ.ም እስከ 14/11/2020 ዓ.ም |
| | | 4 | የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/4173 |
| | | 5 | ዓለም አቀፍ ምድብ- 29፣ 30 እና 32 |
| 6 | የንግድ ምልክቱ የቀለም ዓይነት፣ የብቸኝነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ካለ እና የሚሸፍናቸውን ምርቶች ለማወቅ ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቮልዩም LXXIV ቁ. 303 የወጣውን የምዝገባ ማስታወቂያ ይመልከቱ፡፡ | | |

ምዝገባው ጸንቶ በሚቆይበት ወቅት፣ ባለቤቱን ሳያስፈቅድ፣ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሰራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ላይ በሕግ ክስ እንደሚመሠረትበት እናሳውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት**

**ADDIS ZEMEN VOI-LXXXII No-019 19/1/2015 (29/9/2022)**

### የንግድ ምልክት ምዝገባ እድሳት ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም፡-- ኮርቲና ኤንቪ (CORTINA NV)<br>የአመልካች አድራሻ:Meersbloem-Melden 42, 9700, Oudenaarde, Belgium |
| 2 | የዕድሳት ዘመን፡- ከ 1/09/2013 ዓ.ም. እስከ 1/09/2020 ዓ.ም. |
| 3 | ምልክት- **SAFETY JOGGER** |
| 4 | የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/4393 |
| 5 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡ 9 እና 25 |
| 6 | የንግድ ምልክቱ የቀለም ዓይነት፣ የብቸኝነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ካለ እና የሚሸፍናቸውን ምርቶች ለማወቅ ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቮልዩም LXXVII ቁ. 236 የወጣውን የምዝገባ ማስታወቂያ ይመልከቱ፡ |
| | ምዝገባው ጸንቶ በሚቆይበት ወቅት፣ ባለቤቱን ሳያስፈቅድ፣ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሰራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ላይ በሕግ ክስ እንደሚመሠረትበት እናሳውቃለን፡፡ |

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-019 19/1/2015 (29/9/2022)